የተስፋዬ ጋቢሶ መዝሙሮች

Songs of Tesfaye Gabbiso

የአሳታሚው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው::
All rights reserved.

የተስፋዬ ጋቢሶ መዝሙሮች
(ካሴት ቁጥር 1 እስከ 7)
Songs of Tesfaye Gabbiso
(Cassette # 1 to 7)

የመጀመሪያ እትም ኅዳር 2004 ዓ.ም
የተሻሻለው እትም ግንቦት 2004 ዓ.ም
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
First Printing December 2011
Revised edition May 2012
Addis Ababa, Ethiopia

በኤስ ኣይ ኤም ማተሚያ ቤት ታተመ
Printed by SIM Press

ማውጫ

ገጽ

መግቢያ 4

መቅድም 8

የመዝሙሮች ርእስ ማውጫ 10

ካሴት ቁ 1 13

ካሴት ቁ 2 27

ካሴት ቁ 3 43

ካሴት ቁ 4 59

ካሴት ቁ 5 75

ካሴት ቁ 6 91

ካሴት ቁ 7 106

በፊደል ቅደም ተከተል ለማውጣት 118

መግቢያ

የዚህ ፕሮጀክት ጅማሬ ወደ 40 ዓመታት ይጠጋል። እንደ አዲስ የወንጌል መልእክተኛ፣ በደቡብ ኢትዮጵያ ‹‹አዳዲስ ቤተ ክርስቲያናት›› ዝማሬ ተሳብኩኝ። በ1960ዎቹ የመጨረሻ ዓመታት፣ የቀድሞው ስብሐት ለአምላክ የመዝሙር መጽሐፍ (ከእንግሊዘኛና ከስዊድንኛ የተተረጎሙ መዝሙራት) በስፋት ጥቅም ላይ መዋሉ እየቀነሰ መምጣት ጀምሮ ነበር፣ በምትኩም በኢትዮጵያውያን ወጣቶች ተዘጋጅተው የሚዘመሩ አዳዲስ አገር በቀል ዝማሬዎች እየተበራከቱ መጡ። በ1960ዎቹ መጨረሻ ተስፋዬ ጋቢሶ በአለታ ወንዶ፣ ሲዳሞ ወጣት ተማሪ ሳለ ወደ ሕይወታችን መጣ። የቤተሰባችን፣ በተለይም የሦስቱ ወጣት ወንዶች ልጆቻችን፣ ታላቅ ወዳጅ ሆነ። በብስራተ ወንጌል ሬዲዮ ጣቢያ የሚተላለፉትን አዳዲስ ዝማሬዎች በደንብ ያዳምጥ ነበር፣ በማስታወሻ ደብተሩ ላይም ብዙ መዝሙሮችን ይጽፍ ነበር፣ ደግሞም በአለታ ወንዶ በነበረችው የቃለ ሕይወት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ከጓደኞቹ ጋር ይዘምር ነበር። ከዚያም የማርክሲስት አብዮት ከፈነዳ በኋላ፣ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያናት በመከራ ውስጥ አለፉ። ተስፋዬም በእስር ቤት ውስጥ ብዙ ዓመታትን አሳለፈ። በእነዚያ ዓመታት ውስጥ፣ የተስፋዬ መዝሙሮች ለሁሉም

FOREWORD

The beginning of this project goes back at least 40 years. As a young missionary, I became interested in the songs of the "new churches" in southern Ethiopia. By the late 1960s, the previous wide use of the *Sibhat L'Amlak* hymnbook (translated songs from English and Swedish) was beginning to wane in favor of the wealth of new indigenous songs that were being composed and sung by Ethiopian young people.

Into our lives during the late 1960s came Tesfaye Gabbiso as a young school boy in Aletta Wondo, Sidamo. He became a great friend of our family, especially of our three young sons. He listened avidly to the new music on Radio Voice of the Gospel, wrote down many songs in his notebook, and would sing with his friend at the local Kale Heywet church in Aletta Wondo. Then as the Marxist revolution took hold, the Ethiopian churches suffered, and Tesfaye spent many years in prison. During those years, I discovered how special and precious Tesfaye's songs were to all Christians. Why shouldn't a wider

ክርስቲያኖች እንዴት ልዩ እና ውድ እንደ ነበሩ ተገነዘብኩኝ። ለምንድን ነው እንዲህ የሚባርኩ መዝሙሮችን ቃላት ከኢትዮጵያ ውጭ ያለው የተቀረው ዓለም የማያውቀው? ለሚቀጥሉት 30 ዓመታት፣ የተስፋዬን መዝሙሮች ወደ እንግሊዝኛ የመተርጉሙን ሥራ ስቆጣጠር፣ በኤስ ኣይ ኤም ፕሬስ የነበረው አቶ ኃይሌ ጀናይ ሳይታክት በመተርጎም ጓደኛዬና አበረታቺዬ ነበር። ከልቤ አመሰግነዋለሁ።

በ1990 (እ.ኤ.አ)፣ የተስፋዬ ጋቢሶን መዝሙሮች እንደ ያዝን፣ ባለቤቴ ፖል እና እኔ ለትምህርት ወደ ስኮትላንድ ሄድን፣ እኔም በተስፋዬ ጋቢሶ ዝማሬዎች ውስጥ ያሉ ጥቂት ሥነ መለኮታዊ ጭብጦችን ለማጥናት በኤድንበርግ ዩኒቨርስቲ ውስጥ ባለው በኒው ኮሌጅ የአፍሪካውያን ሥነ መለኮት ክፍል አስተማሪ በነበሩት በፕሮፌሰር ጆን ፓራት ተበረታታሁ። ይህም ጥናት "Theology in Song: Ethiopia's Tesfaye Gabbiso" ወይም ‹‹ሥነ መለኮት በዝማሬ፡- ኢትዮጵያዊው ተስፋዬ ጋቢሶ›› የሚሰኝ መጣጥፍ ወጣውና በ1997 እ.ኤ.አ) በታተመው "Missiology, An International Review" መጽሔት ላይ ታተመ።

በ2008 (እ.ኤ.አ)፣ የኤስ ኣይ ኤም ሥነ ጽሑፍ ክፍል ኃላፊ ከሆኑት ከአቶ ዘነበ ገብረሐና፣ የኤስ ኣይ ኤም (ሚዲያ አስተባባሪ ከሆኑት ከሚ/ር

world outside Ethiopia know the words to songs that were such a blessing? Over the next 30 years, as I slowly supervised the translation of Tesfaye's songs into English, Ato Haile Jenai at the SIM Press in Addis Ababa was a tireless translator, colleague and encourager. I thank him most heartily.

In 1990, with Tesfaye Gabbiso's songs in hand, my husband Paul and I went to study in Scotland, and I was encouraged by Professor John Parratt in an African Theologies class at New College, University of Edinburgh, to study some of the theological themes in the songs of Tesfaye Gabbiso. This study resulted in a seminal article "Theology in Song: Ethiopia's Tesfaye Gabbiso" published in 1997 in *Missiology, An International Review.*

During 2008, in consultation with Ato Zenebe Gebrehana (SIM Media director), Mr. Fred McGinley (SIM) and Pastor Tesfaye Gabbiso, we made the decision to publish a diglot of the songs in both Amharic and English. As is well known, it is very difficult to translate poetry from one language to another. This translation has endeavored to capture the essence and meaning of

ፍሬድ ምክኒንሊ እና ከመጋቢ ተስፋዬ ጋቢሶ ጋር በመመካከር፣ መዝሙሮቹን በአማርኛ በእንግሊዝኛ ጎን ለጎን ለማሳተም ወሰንን። እንደሚታወቀው፣ ግጥምን ከአንዱ ቋንቋ ወደ ሌላው መተርጎም በጣም አስቸጋሪ ነው። ይህ የትርጉም ሥራ የመዝሙሮቹን ፍሬ ነገርና ትርጉም ለመጠበቅ ሞክሯል፣ ቢሆንም ግን በእንግሊዝኛ ሊዘመር የሚችል ትርጉም አይደለም።

ከሚከተሉት ምክንያቶች የተነሣ፣ ይህ መጽሐፍ ጠቃሚ ነው፦

1. ከቀድሞዎቹ አገራዊ ዝማሬዎች መካከል ወይ የሆኑትን ዝማሬዎች በጽሑፍ በማስቀረት ወደ ፊት በመስኩ ጥናት ለሚያደርጉት ኢትዮጵያውያን ምሑራን የመረጃ ምንጭ ማዘጋጀት።
2. በአብዮቱ ጊዜ በተስፋዬ ዝማሬዎች በጣም ተባርከው ለነበሩት ለአሁኖቹ የአንጋፋዎቹ ትውልድ የመዝሙር የጥሞና መጽሐፍ ማቅረብ።
3. የእነዚያን መዝሙሮች ትክክለኛ ቃላት በጽሑፍ በማስፈር የወጡ ትውልድ ዘማሪዎች በአሁኑ ጊዜ የሚያቀነባብሯቸውን መንፈሳዊ መዝሙሮች ይዘት ማጠናከርና ማሳደግ እንዲችሉ መርዳት።
4. ለተማሪዎች፣ በቋንቋ ትምህርት ላይ ላሉ ሚሲዮናውያን፣ እና

the songs, but it is not a translation that could be sung in English.

For the following reasons, this book is important:

1. To capture a representation of the earlier indigenous songs in print so as to make available archival resources for future Ethiopian scholars.
2. To provide a devotional book of songs for today's older generation who were so blessed by Tesfaye's songs, especially during the revolution.
3. To record in writing the actual words of those songs as a catalyst to the younger generation of musicians to strengthen and enhance the content of the spiritual songs presently being composed.
4. To offer an English-Amharic (both ways) language-learning aid for students, missionaries in language learning, etc. (Singing out of the *Sibhat L'Amlak* hymnal week by week in my early years as a missionary was a very important language-learning tool.)
5. To bless not only the world-wide diaspora of Ethiopians who are nurtured by songs of their motherland but also Christians of

ለሌሎችም የእንግሊዝኛ-አማርኛ (በሁለቱም አቅጣጫ) ቋንቋ መማሪያ መርጃ መሣሪያ ማቅረብ። (በሚሊዮናዊነቴ የመጀመሪያዎቹ ዓመታት ወቅት ከስብሐት ለአምላክ የመዝሙር መጽሐፍ መዘመር ለእኔ በጣም ጠቃሚ የቋንቋ-መማሪያ መሣሪያ ነበር።)

5. በእናት አገራቸው መዝሙሮች የታነጹትን በመላው ዓለም የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ዲያስፖራዎችን ብቻ ሳይሆን፣ ነገር ግን ይበልጥ ግሎባላይዝድ እየሆነች በመጣችው ዓለማችን ውስጥ በሚገኙ ብዙ ባህሎች ውስጥ ያሉ ክርስቲያኖችን ጭምር ለመባረክ።

6. የኢትዮጵያን አዳዲስ ቤተ ክርስቲያናት ዝማሬዎች መንፈሳዊነት ለሁሉም ሃይማኖታዊ ትውፊቶች (ልማዶች) ለማካፈል።

ከላይ ከተጠቀሱት ስሞች በተጨማሪ፣ ይህንን ልዩ መጽሐፍ በማረም፣ የኮምፒዩተር ጽሑፍና የገጽ አቀማመጥ ሥራ በማከናወን፣ እንዲሁም በጎ-መት ሥራው የተሳተፉትን የኤስ ኣይ ኤም ሚዲያ ሠራተኞች በሙሉ ለማመስገን እፈልጋለሁ። ይህ ባለ ሁለት ቋንቋ የመዝሙር መጽሐፍ ለእግዚአብሔር ክብር እንዲያመጣ እና ለብዙዎችም መጽናኛ እንዲሆን ጸሎታችን ነው።

ሚስስ ላይላ ባልስኪ
Grand Prairie AB T8V 4A5
Canada
Email: paulilab@telus.net

many cultures in our increasingly globalized world.

6. To share with all religious traditions the spirituality in song of Ethiopia's new churches.

In addition to names listed above, I wish to thank all those at SIM Media who have assisted in the editing, formatting, and production of this unique book. Our prayer is that this diglot of songs will bring glory to God and be an encouragement to many.

Mrs. Lila W. Balisky
Grande Prairie, AB T8V 4A5
Canada
Email:-
paulilab@telus.net
January 2011

መቅድም

ከተስፋዬ ጋር የተዋወቅነው በ1967 ዓ.ም ነበር። በዚያን ጊዜ ዕድሜው ከ20 ዓመት የማይበልጥ የ2ኛ ደረጃ ተማሪ ሲሆን፣ ያኔም መዝሙር ይጽፍና ይዘምር ነበር። የመዝሙሮቹ አሳብ ጥልቀት፣ የቅኔው ውበት፣ የቋንቋው ጥራት፣ የዜማው አሪጅናልነትና የድምፁ ልዝብነት በእርሱ ዕድሜ ካለ-አማርኛም አፍ መፍቻው ካልሆነ-ወጣት የሚጠበቅ ዓይነት አልነበረም። እና ተስፋዬና መዝሙሮቹ በእምነታችን ገና ጨቅላ የነበርነውን የእኔንና የባለቤቴን፣ የገነትን፣ ቀልብ የቀለቡት ሲዘምራቸው ከሰማንበት ከመጀመሪያዋ ምሽት ጀምሮ ነበር።

ብዙም ሳይቆይ፣ የይርጋለም ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን መዝሙሮቹን በኦዲዮ ካሴት ማስቀረጽና ማሰራጨት ጀመረች። በ1971 ዓ.ም ተስፋዬ ከመታሠሩ በፊትም ከአንድ እስከ ሦስት ቁጥሮች ድረስ ያሉት ካሴቶቹ በተከታታይ ወደ ኢትዮጵያ ወንጌላውያን ምእመናን እጅ ሊገቡ ቻሉ። ቀደም ሲል ተ ቀርጾ ስለ ነበረ፣ ቁጥር አራትም ወዲያው ተከተለ። የትንቢታዊ መዝሙሮቹ «ቃል» በመጀመሪያ በራሱ ሕይወት «ሥጋ» ይሆን ዘንድ ተስፋዬም ወደ ወኅኒ ተጣለ። እኛም እነዚያን የመከራ ዓመታት በተስፋና በእምነት፣ በጸሎትና

Preface

It was in 1974 G.C. that we were acquainted with Tesfaye. He was a 20 year old High School student, and even at that time, he used to write hymns and sing them. The depth of the hymns' idea, the beauty of the poetry, the language clarity, the originality of the songs, and the softness of his voice was unexpected from some one of his age- from a youngster for whom Amharic is not his mother–tongue. Tesfaye and his songs got my wife's and my attention since that first night we heard him sing them- we were spiritual babies at that time.

Soon, Yirgalem Full Gospel Believers' Church started to put his songs in audio - cassettes and distribute them. His Cassettes #1 up to #3 managed to be in the hands of Ethiopian Evangelical believers before he was imprisoned in 1978 G.C. Since it was already recorded, Cassette #4 was out very soon. For the "word" of his prophetic songs to be "flesh" in his own life, Tesfaye was thrown in prison. God blessed us abundantly by those songs so that we could pass those years of suffering with hope and faith, as well

በጽናት፣ እናልፋቸው ዘንድ እግዚአብሔር በእነዚህ መዝሙሮች በብዙ ጠቀመን።

with prayer and perseverance.

አሁን እንደምናየው ደግሞ፣ እግዚአብሔር በተስፋዬ መዝሙሮች ከጠቀማቸው መካከል እነ ላይላም ለካ አሉበት! በዚህ መድብል ውስጥ እኅታችን ላይላ ባልስኪ መጋቢ ተስፋዬ ጋቢሶ ከተፈታ በኋላ የዘመራቸውንም መዝሙሮች አካትታቸዋለች። ክብር ለአምላካችን ይሁን! አሜን።

As we can see now, God was using Tesfaye's songs to minister even to people like Lila! In this book, Lila Balisky has also incorporated those songs which Tesfaye Gabisso sang after he was freed from prison. Glory be to Our God! Amen.

መጋቢ በቀለ ወልደ ኪዳን
የሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን

Bekele Woldekidan (Pastor)
Full Gospel Believers' Church

የተስፋዬ ጋቢሶ በየካሴቶቹ ውስጥ ያሉ መዝሙሮች በርእስ ማውጫ

ካሴት ቁጥር 1

ለእኔም አባቴ ሆይ 1-1
በከፍታ ስፍራ በሰማይ ያለኸው 1-2
ኃጢአት ሥሩን ሰዶ ሳይጠነክርብኝ 1-3
እንባዬን አይተህ፣ ጌታ 1-4
የባዘነውን ፈላጊ አምላክ 1-5
ተመለስ፣ ተመለስ 1-6
ልጅነቴ ያላለቀ 1-7
በጊዜውም አለጊዜውም 1-8
ዝም ብዬ እቆማለሁ 1-9
ምስጋና የሚገባውን 1-10
እግዚአብሔር ኃያል 1-11
የማይናወጥ መሠረቴ 1-12
እታገላለሁ 1-13
እምቢ አሻፈረኝ 1-14

ካሴት ቁጥር 2

የምስራች ቡሉ 2-1
አስብበት ዛሬ 2-2
ጌታ ኢየሱስ፣ አትተወኝ 2-3
እንዲህ አልነበርኩም 2-4
በጭንቄ ተጨንቆ፣ መስቀል ላይ ተሰቅሎ 2-5
በአምላክ አምሳል 2-6
ተጠፍሬ ያየኝ 2-7
እንዘምራለን 2-8
ተመስገን ጌታዬ 2-9
ላመሰግንህ ዛሬ 2-10
የእኔ ጌታ ስለ እኔ ገደት 2-11
በሰማይ በምድርም ሙሉ ሥልጣን ያለው 2-12
አትጠራጠረው 2-13
የፍጥረት ገዢ ተቆጣጣሪው 2-14
አየሁ 2-15

ካሴት ቁጥር 3

እኔ ነኝ ተራራው 3-1
ስብራቴ የማይፈወስ ይመስላል 3-2
ኢየሱስ፣ የነፍሴ መድኃኒት 3-3
ጠላቴ ሆይ፣ ብወድቅ እነሣለሁኝ 3-4
የሠራልኝን ድንቅ 3-5

መነቀፍን ፈርቶ 3-6

Tesfaye Gabbiso – Titles by Cassettes

CASSETTE 1

Dear Father 1-1
You Who Are in the High Place 1-2
Before Sin Sends and Strengthens Its Roots 1-3
Seeing My Tears, Lord 1-4
God Who Searches the Stray 1-5
Come Back, Come Back 1-6
My Infancy Is Not Yet Over 1-7
In Season and Out of Season 1-8
I am Simply Standing 1-9
I Will Call on God 1-10
God Is Mighty 1-11
My Unshakable Foundation 1-12
I Will Struggle 1-13
I Refuse, I Refrain 1-14

CASSETTE 2

Tell the Good Tidings 2-1
Think About It Today 2-2
Lord Jesus, Do Not Leave Me 2-3
I Was Not Like This 2-4
Hanging On the Cross 2-5

I Was Created in God's Likeness 2-6
The One Who Saw Me Tied Up 2-7
Sing For Our God 2-8
Be Praised, My Lord 2-9
Let Me Thank You Today 2-10
My Lord Was Concerned About Me 2-11
He Who Has All Power 2-12

Do Not Doubt Jesus 2-13
The Ruler and Controller of Nature 2-14
I Saw 2-15

CASSETTE 3

I Am the Mountain 3-1
My Brokenness Seems Non-repairable 3-2
Jesus, Cure of My Soul 3-3
O, My Enemy, If I Fall 3-4
Let Me Tell You the Wonderful Story 3-5
Afraid of Criticism 3-6

ሥጋን ነፍሱን ጠልቶ 3-7	Flesh Is Reviving 3-7
ዘመኑ ፈጠነ 3-8	The Season Speeded 3-8
ያ ተንከራታቹ 3-9	That Wanderer 3-9
ባስቀመጥከኝ ቦታ ጸንቼ አንድቆይህ 3-10	That I May Stay Firmly 3-10
በትዕግሥት ፀጥታ 3-11	In Patient Quietness 3-11
እስከ ዛሬ የጠበቅከን 3-12	You Who Watched Over Us Until Today 3-12
አንተን፣ አንተን ብዬ 3-13	Seeking You and You First 3-13
ኢየሱስን ለብሰህ 3-14	Putting On Jesus 3-14
ልብህ ጽኑ ይሁን 3-15	Let Your Heart Be Firm 3-15
ለረጅም ዘመናት 3-16	After Suffering and Languishing 3-16
ካሴት ቁጥር 4	**CASSETTE 4**
መልክህን ጌታዬ 4-1	Your Beauty, My Lord 4-1
የባዘንከው ውድ ወንድሜ 4-2	You Who Wander 4-2
ከሸካራው መንገድ እግርህን መልሰው 4-3	Retreat From the Rough Road 4-3
ሊጠፋ ነበር፣ በጋጢአቱ ረክሶ 4-4	The One Who Was About to Be Lost 4-4
የዘላለም አምላክ፣ የዘመናት ንጉሥ 4-5	God of Eternity and King of the Ages 4-5
የፈርዖን ገንዘብ ያልማረከው ጀግና 4-6	The Hero Who Was not Attracted by Pharaoh's Riches 4-6
አ፣ ክብር 4-7	O, Glory 4-7
ምስጋና ይገባሃል፣ የሠራዊት ጌታ 4-8	You Should Be Praised, Lord of Hosts 4-8
ሕዝብን አበዛህ 4-9	You Multiplied Your People 4-9
ምሕረቱ አያልቅምና 4-10	His Mercy Is Everlasting 4-10
ከአቅምህ በላይ ሆኖ የሚከብድህ? 4-11	What Is Heavy and Beyond Your Ability? 4-11
ኃይልህን ቀምሼ 4-12	After Tasting Your Power 4-12
መብዛት መዋረዱን፣ መራቡን መጥገቡን 4-13	To Be in Need, To Have Plenty 4-13
በእውነት እኖራለሁ 4-14	I Live by Faith 4-14
ለእኔም ያንን ጸጋ በሕይወቱ አምቂ 4-15	Keeping That Grace in My Life for Me 4-15
እኛ ግን የሞተልንን 4-16	The One Who Died for Us 4-16
ካሴት ቁጥር 5	**CASSETTE 5**
በኩርነትህን ለምን ሸጥከው? 5-1	Why Did You Sell Your Birthright? 5-1
አንተ የምትተኛ 5-2	You Who Fall Asleep 5-2
የአደባባይ ሰው 5-3	Oh, You Street Man 5-3
መቼ ነው ነቅቼ ድምፅህን የምሰማው? 5-4	When Will I Hear Your Voice? 5-4
ከእግርህ ሥር መሆን ግሩም ነው 5-5	It's Wonderful to Be at Your Feet 5-5
በእምነት አሳድገን 5-6	Oh, Lord, Cause Us to Grow in Truth 5-6

ግን አንድ ነገር አውቃለሁ 5-7	But I Know One Thing 5-7
የናዝሬቱ ኢየሱስ 5-8	Jesus of Nazareth 5-8
ነፍሴ ሆይ፣ እግዚአብሔር አምላክ	O, My Soul, He is the Lord;
ነውና ስገጂለት 5-9	Worship Him 5-9
ለአምላካቸው በቀር 5-10	Other Than Their God 5-10
እግዚአብሔር ሲረዳ 5-11	When God Assists 5-11
ሊኖሩ የሚወዱ ሁሉ 5-12	All Those Who Wish to Live 5-12
ተነሥ፣ ተነሥ 5-13	Rise Up, Rise Up 5-13
የሚቋቋምህ ማንም የለም 5-14	There's No One Who Can Challenge You 5-14
ነፍሴ ወደ አምላኪ 5-15	Before My Soul Returns to Her God 5-15
አባታችን ሆይ! 5-16	The Lord's Prayer 5-16
ካሴት ቁጥር 6	CASSETTE 6
የልቤ አምላክ ሆይ 6-1	O, God of My Heart 6-1
እጁን ዘርግቶ 6-2	If His Hand Was not Stretched Out 6-2
ጠቢብ በጥበቡ አይመካ 6-3	Let Not the Wise Be Proud in His Wisdom 6-3
አዲስ ዝማሬ 6-4	A New Song 6-4
እንደ ተቀበልኩት ምሕረት 6-5	According to the Mercy I've Received 6-5
አቤቱ፣ መባረክን ባርከን 6-6	Oh Lord, Bless Us with a Blessing 6-6
በእምነት ድል እየነሡ 6-7	Winners Through Faith 6-7
አምላኬ፣ አምላኬ 6-8	My God, My God 6-8
ማሰሮ ሲሰበር 6-9	When the Pot Breaks 6-9
በፍጹም ልባቸው እንዲያገለግሉት 6-10	That They Serve Him 6-10፤
ፈቃድህን እንዳደርግ 6-11	To Do Your Will 6-11
የአምላኩ ፈቃድ 6-12	Allowing the Will of His God 6-12
ደስ ይበልህ ወንድሜ 6-13	Be Glad, My Brother 6-13
ርስትህን ለማላገጫ አሳልፈህ አትስጥ 6-14	Do Not Turn Your Inheritance Over to Mockery 6-14
ና ጌታዬ፣ ጌታ ሆይ 6-15	Oh, Lord, My Lord, Come 6-15
ካሴት ቁጥር 7	CASSETTE 7
ያይሃል 7-1	He Sees You 7-1
የኃጢአተኛውን ጥፋት 7-2	When Would God ever Want the Sinner to Perish? 7-2
ቤዛ የሆንክልኝ 7-3	You Became My Redeemer 7-3
ቃሉን ከቶ የማያጥፍ 7-4	He Never Breaks His Promises 7-4
አቤቱ፣ ጌታችን 7-5	O Lord, Our Lord 7-5
ባለፍክበት መንገድ 7-6	On Whatever Road I Walked 7-6
የጸሎት ቤት ይሁን 7-7	May Your Temple Be a House of Prayer 7-7
ማደሪያዎችህ 7-8	Your Dwelling Places 7-8
የጠፋውን ማን ይፈልጋል? 7-9	Who Would Seek the Lost? 7-9
ፍቅር ነው የጐደለኝ 7-10	It's Love That I Lack 7-10
ኢየሱስ ክርስቶስ 7-11	Jesus Christ 7-11
ከዚህም የሚበልጥ 7-12	Greater Things than This 7-12

ካሴት ቁጥር 1
I-1

ለኔም አባቴ ሆይ

ለኔም አባቴ ሆይ፣ ልቤን ስበርልኝ፣
እኔነቴ ደቆ ጸጋ እንዲበዛልኝ፣
ትእቢቴን ሽረህ ትሕትናን ስጠኝ።። } አዝ (2x)

1. መዋረዳቸውን አይተህ አንተ ባርከሃቸው፣
የቤትህን ልጆች አንተ ሰብረሃቸው፣
ትቢታቸው ጠፍቶ ከትሑት ልባቸው፣
እንባቸውን ሲያፈሱ ለምተው አየኋቸው።።

2. እቃትታለሁኝ ዘወትር መሰበርን ሽቼ፣
አብዝቼ እጮሃለሁ ሌት ተቀን ተማቼ።።
እስክ መቼ ድረስ ሕይወቴ እንዲህ ደርቆ፣
እኖራለሁ፣ ጌታ፣ ልምላሜ አልቆ።።

አዝማች. . . (2x)

3. የመሰበር ፍላጐቴ ግለቱ ሳይበርድ፣
ሰማዮችን ቀድደህ ምነው ብትወርድ?
ጉጉቴን መዝነህ አባክህ ስበረኝ፣
ትሑትና ታዛዥ መሆንን አስተምረኝ።።

አዝማች. . .(2x)

4. የራሴን ማንነት ያኔ በርግጥ እረዳለሁ፣
የውስጥ ዓይኔ በርቶ አጥርቼም አያለሁ።።
በፍጹም ግልጽነት ስምህን አውጃለሁ፣
በበረከት መላት አስክብርሃለሁ።።

አዝማች. . .(2x)

CASSETTE 1 - ENGLISH TRANSLATION

Song 1-1
Dear Father

CHORUS:
Dear Father, break my heart too
So that the self may be crushed and grace may abound to me.
Cancel out my pride; give me meekness.

1. Seeing that they are humiliated, bless them.
Making the children of Your house humble
With pride destroyed and a meek heart,
I saw them simply shedding their tears.

2. I'm always moaning, seeking that meekness.
I'm crying a lot, day and night.
For how long will my life stay dry like this?
I'm living, Lord, with the lushness of my life dried up.

3. Before my deep desire for brokenness declines,
Why don't You rend the heavens open and come down.
Consider my wish; please break me.
Teach me humbleness and obedience.

4. I will then know for sure who I am.
I will see clearly when my internal eyes get bright.
I will proclaim Your name with great boldness.
I will glorify you with full blessings.

I-4

እንባዬን አይተህ፣ ጌታ

እንባዬን አይተህ፣ ጌታ፣
ለቅሶዬን ሰምተህ፣ ጌታ፣
መሻቴን ስጠኝና፣
የሱስ ላመስግንህ።።

አዝ (2x)

1. አንድን ነገር ሽቼ ደጅ አጠናለሁኝ
ፈቃድህ ከሆነ በዓይንህ ተመልከተኝ
ያቺን ብሩክ እጅህን ዘርጋብኝ።።
2. አንተን ተስፋ አድርጌ
በቃልህ ጸንቼ፣
መልሴን እጠብቃለሁ
በተመስጦ ሆኜ፣
ታማኝነትህን ተማምኜ።።

አዝማች. . .(2x)

3. በጐ ስጦታና ፍጹም በረከት ሁሉ
ከብርሃን አባት ከላይ ይወርዳሉ፣
ከዙፋንህ ይንቆረቆራሉ።።

አዝማች. . .(2x)

4. መራራነቴ ያብቃ
እሾህነቴም ያብቃ።።
መፈራረሴም ያብቃ
በንተ ጸጋ ልገንባ
ጕስቁላነቴን፣ ጌታ፣ ሆይ እንካ።።

አዝማች. . .(2x)

Song 1-4

Seeing My Tears, Lord

CHORUS
Seeing my tears, Lord,
Hearing my cry, Lord,
Give me my desire.
And I will praise You, Jesus.

(2x)

1. Wishing one thing, I am patiently waiting on You.
If it is your will, look at me with your eyes.
Stretch out that blessed hand of Yours.

2. Putting my hope on You, strengthening myself in your word,
I am waiting the answer, while in a trance,
Depending on Your faithfulness.

3. All the good gifts and perfect blessings – They come down from the Father of light, above.
They pour down from Your throne.

4. May my bitterness and my thorniness be finished.
May my wreckage be stopped and may I be built by Your grace.
Oh, Lord, just take away my wretchedness.

I-5

የባዘነውን ፈላጊ አምላክ

የባዘነውን ፈላጊ አምላክ
የምሕረት አምባ፣
ለጠፉትም የምታነባ
ከሕይወት ወደ ሞት፣
ከዕረፍት ወደ ጭንቀት፣
የሄደውን መልስ አባክህ ጌታ
ወደ መንጋህ በረት

አዝ (2x)

1. የጠራውን መስሉ መኖር
መጋደሉን ፈርቶ፣
የገባለትን ቃልና ተስፋውን ዘንግቶ፣
የሞት ልጅ የነበረ ሰው
ከጥፋት የዳነው
የተሠዋለትን ኢየሱስ
ያን አዳኙን ክዳው።።
2. ተዋግቶ የማረከውን
ያን ስመ ጥር ጀግና፣
ጌታውን ሊያስከብር
ቆርጦ ተሰልፏልና፣
ጠላት ከባሻገር ቆሞ
ቅናት እያጋየው፣
አሸክላውን ዘርግቶበት
ወንድሜን ጠለፈው።።
አዝማች. . .
3. በአምላኩ መቅደስ ውስጥ ሆኖ
ተማምኖ እያገሳ፣
ግናናነቱንም ሊያውጅ
የይሁዳን አንበሳ፣
እንግዳ ነገር ወሰደው
ነዝንዝ ጨቅጭቆ
ጸጋ ክብሩን አስላጭቶ
እጅግ አስጨንቆ።።
አዝማች. . .
4. ጥቃቅኑ ነገር ሁሉ
ጉልበቱን ከርክሮት፣
ጤናውን እየሰረቀበት
በሕመም አደንዝዞት፣
ያ የክሕደት አውሎ ነፋስ
በሕይወቱ ነፍሰበት፣
ከወይኑ ግንድ ገነጠለው
ፍሬ እንዳይገኝበት። (አዝማች. . .)

Song 1-5

God Who Searches the Stray

God, who searches the stray
Mount of mercy,
You who weep for the lost
Call back the one who went
From life unto death,
From rest into depression.
Please return him, Lord,
Back to the barn of your flocks.

chorus

1. Fearing to live in the likeness of his Lord and to struggle
Forgetting the one who gave him promise and hope,
That person, who was the child of death
And who was delivered from destruction
Denied the one who delivered him from destruction
And the one who was crucified for him.
That was Jesus – his Savior, whom he'd denied.

2. The Lord, that famous hero, who fought and captured
That warrior who decisively stood to
The enemy, standing at the other end.
Burning with jealousy
Spreading his net before,
My brother, and captured him.

3. Inside his God's temple
Confidently roaring
As he proclaims the fame of
Judah's lion
Strange thing took him away by nagging
Shaving off his grace and honour
With great distress.

4. Oppressing in everything
Challenging his strength,
Stealing his health from him
Numbing him by disease,
That whirlwind of denial (atheism)
Blowing on his life –
It cut him off the vine
So that he won't bear any fruit.

I-6

ተመለስ፣ ተመለስ

ተመለስ፣ ተመለስ፣ ተመለስ፣
ልጄ ሆይ።
ተመለስ፣ ተመለስ፣ ተመለስ፣
ልጄ ሆይ።

} አዝ.

1. ተስፋህ ጨልሞ፣
ጭንቀት አስጥሞህ፣
መጥፋትህ ታይቶኝ ከዚያ ጣር
አውጥቼህ፣
ደስ ብሎህ ነበር አግኝተህ እፎይታ፣
ለምነው ዛሬ የሆንከው ከርታታ።
አዝማች. . .

2. በእኔ ተማምነህ ስትመላለስ፣
በእንባ በጸሎት ቀርበህ ታደስ፣
የነበረህ ወዝ መልክህስ የታለ?
ናና ታረቀኝ ጸጋዬ እያለ።
አዝማች. . .

3. የፍቅርን ወንጌል ስለሰው ሰብከህ፣
ሸክማቸው ከብዶህ ለጠፉት አልቅሰህ፣
መስክርህ ወደ ሕይወት አምጥተህ፣
ሳይህ አዝናለሁ አንተ ግን ኮበልለህ።
አዝማች. . .

4. ቤቴ ናፍቆህ ብትመለስልኝ፣
ይቅርታህን ፈልገህ ብትመጣልኝ
የምሕረት እጄ ተዘርግታለች፣
የፍቅር እንባም ዓይኔ ታፈስሳለች።
አዝማች. . .

Song 1-6

Come Back, Come Back

CHORUS:
Come back, come back, come back,
oh, My child
Come back, come back, come back,
oh, My child.

1. Seeing you hopeless
Sunk in depression and lost
I had saved you from that pain
You felt happy by getting relief
But then what made you a wanderer to-day?

2. When you walked putting your trust in Me
In tears and prayers your strength got restored
But where is that grace and beauty now?
Come, come , be My friend while my grace is present.

3. You preached the gospel of love to others
You felt their burden and wept for the lost
By your testimony you brought them to life
Oh, I am sorry but you have gone astray.

4. Being homesick for My house,
If you would come back to Me
Asking for pardon, if you would come to Me,
My hand of mercy is stretched out
And My eyes are shedding tears of love.

I-7

ልጅነቴ ያላለቀ

ልጅነቴ ያላለቀ
ነኝና ብላቴና።
ሙሉ ሰው አድርገኝ፣ ጌታ
ቃልህን አብላኝና።

አዝ. (2x)

1. በግብዝነት ተሯሩጬ
ከእውነትህም ተሳስቼ፣
በስሜቴ ተገፋፍቼ፣
የቃልህን ሙላት አጥቼ፣
እንዳልጠፋ በጠላት ተጠቅቼ።
አዝማች. . .(2x)
2. ለጋነቴ እኔን አጋልጦኝ፣
መከራውም አጠውልጐኝ፣
ዐውሎ ነፋስ አፍንጭግሞኝ፣
የአሸዋው መሠረት አዝሞኝ፣
ከፉኖ ገፍትሮ እንዳይጥለኝ ::
አዝማች. . .(2x)
3. ወተት ብቻ መጋቱን ትቼ፣
አጥንቱንም ደግሞ በልቼ፣
እንደ ሕፃን ማሰቤ ቀርቶ፣
በጕልማሳነት ተተክቶ፣
ላይህ አሻለሁ ሕይወቴ ተገንብቶ።
አዝማች . . . (2x)

Song 1-7

My Infancy is not Yet Over

CHORUS:

My infancy is not yet over.
I am still an infant.
Feed me Your word, Lord,
And make me a full-grown man.

1. Running in hypocrisy,
Getting diverted from Your truth,
Being pushed by my emotions,
Lacking the fullness of Your word,
Lest I perish, attacked by the enemy.

2. My youth exposes me
And misery withers me;
The whirlwind tosses me around,
The foundation of sand is sinking me,
Lest it knocks me down, help me.

3. Ceasing from drinking only milk
And also gnawing at bones;
And ceasing to think like a child
Replaced by adulthood;
I would like to see my life developed.

I-8

በጊዜውም አለጊዜውም

አዝ. በጊዜውም አለጊዜውም
በስምህ ጸንቼ ቆሜ።
ፊትህን ለማየት እጓጓለሁ
እሩጫዬን ፈጽሜ።
ስለዚህ ፍቃድህ ይሁንልኝ፣
ውድ አባቴ፣
በሰላም በጤና አድርሰኝ ክቤቴ።

1. የጠላቴን ራስ ቀጥቅጠህ
ከመንጋጋውም እኔን ነጥቀህ
ቅዱስ ደምህን አፍሰህ
ለሙት ልጅህ ሕይወት ሰጥተህ
ታላቁን ሥጋ ድኛለሁ
አሁንም መጽናናት አግኝለሁ።
አዝማች. . .

2. ስቅበጠበጥ መክረኸኛል
ስተክዝ አጽናንተኸኛል
ባቆስልህም ወደኸኛል
ዘወትር ተሸክመኸኛል
እስከ ዛሬ ችለኸኛል
ቅዱስ ስምህ አቁሞኛል።
አዝማች. . .

3. ዘወትር በሁሉም ስፍራ
አንተን ልምሰል፣ አንተን ልፍራ፣
ከዓለም አድርገኝ ልዩ
በኔም ሕይወት አንተን ይዩ።
ሥጋዬን ለዓለም ሰቅዬ
ልጓዝ አንተን ተከትዬ።
አዝማች. . .

4. በድካም ሕይወቴ ላልቶ፣
አካሄዴም ተበላሽቶ።
ቅዱስ ስምህ እንዳይሰደብ፣
አደራህን ልጅህን አስብ።
እስክትመጣልኝ በክብር፣
አንተን አስከብሬ ልኑር።
አዝማች . . .

5. በከፍታም በዝቅታም፣
በኀዘንም በደስታም፣
ሳልደናገር በርጋታ
በፈተናም ሳልረታ፣
በትጋት ጸንቼ በምድር
ፊትህን ልየው በክብር። (አዝማች)

Song 1-8

In Season and Out of Season

CHORUS:

In season and out of season
Standing strong in Your name
I long to see Your face
After completing my race.
So may it be Your will, my dear Father,
Cause me to reach my home in peace and health.

1. Bruising my enemies' head
Snatching me out of his jaws
Shedding Your holy blood
Giving life to Your dead child
I experienced the great salvation
And now I want to be strong.

2. When I was restless, You gave me advice.
When I was sad, You comforted me.
Even though I wounded You, You loved me.
And You have always been patient with me.
You tolerated me until this day,
Your holy name sustains me.

3. Always and at all places
Let me be like You and fear You.
Make me different from the world
Let them see You through me.
Let me crucify my body for the world;
Let me travel following You.

4. My life being loose because of fatigue
And my walk being spoiled,
Lest Your name be insulted,
I beseech You, think about Your child
Until You come for me in glory,
May I live honoring You.

5. In height and depth,
In sorrow and in happiness,
Without being confused, but in calmness,
Not being defeated by temptations
May I be steadfast and diligent in this world
Let me see Your face in glory.

I-9

ዝም ብዬ እቆማለሁ

ዝም ብዬ እቆማለሁ
ሰልፉን ለአንተ አለቃለሁ::
በእምነት ወደ አንተ አያለሁ
ጌታ ሆይ፣ ድልህን እጠብቃለሁ::

} አዝ. (2x)

1. በዚች ምድር ላይ ብርቱ ሰልፍ አለብኝ፣
እኔ ዝም እላለሁ፣ አንተ ተዋጋልኝ::
አንተን ያሰለፉ ትግሉ ሰምሮላቸው፣
አይቼ ተምሬያለሁ ከድል ዝማሬያቸው::
አዝማች. . .

2. ሰልፉ የእኔ መስሎኝ እረታለሁ ብዬ፣
በሥጋዬ ስታገል፣ ተዝለፍልፌ ዝዬ::
መረታቴ ነው እኮ፣ ኢየሱስ ጌታዬ::
ኧረ፣ ቶሎ ናልኝ፣ አይብዛ መከራዬ::
አዝማች . . .(2x)

3. የሰላት ሰረገላው፣ መለኮታዊው ጦር
የድምፅህ ነጐድጓድ ጠላት የሚያሸብር
ይምጣ ይዋጋልኝ፣ እኔ ኃይል የለኝም፣
አሁን አውቄያለሁ፣ ሰልፉ የኔ አይደለም::
አዝማች. . . (2x)

Song 1-9

I Am Simply Standing

CHORUS:
I am simply standing;
I am leaving the battle to You.
I look by faith unto You;
O Lord, I am waiting, watching
for your victory.

} (2x)

1. On this earth I am facing a great battle
I'll keep quiet. You fight for me.
I have seen the successful fight of those who extol You.
And I have learned that from their triumphant song.

2. Thinking the battle was mine and saying "I will win"
When I was fighting with my flesh, I was faint and weary.
I am about to be defeated, Jesus my Lord.
Oh, please come quickly, don't let my troubles increase.

3. Chariots of fire, that divine army
The sound of thunder that panics my enemies
Let Him come and fight for me, for I have no strength.
Now I know that the battle is not mine.

I-10

ምስጋና የሚገባውን

ምስጋና የሚገባውን
እግዚአብሔርን አጠራዋለሁ
ከጠላቶቼም እድናለሁ።
} አዝ. (2x)

1. የዐመፅ ፈላሽ ሲያስፈራኝ
የሲኦል ጣርም ሲከበኝ
አምላክህ የታሰ ሲለኝ
ባላንጣዬ ሲያፌዝብኝ
ከመሠረቴ ሊነቅለኝ
ቆይ ብቻ ሲል ሲዝትብኝ
የጌታን ስም እጠራለሁ
ከጠላቴም እድናለሁ።
አዝማች. . . (2x)

2. የጌታ ኢየሱስ ስም ለእኔ
የጸና ግንብ ነውና፤
እስከ ዛሬም እርሱን ጠርቶ
ማንም አላፈረምና፤
በኪሩቤል የሚኖረው
መሱ ተስፋ ስለ ሰጠኝ፤
ታምኜ ስሙን እጠራለሁ
ከጠላቴም እድናለሁ።
አዝማች. . . (2x)

3. በጨነቀኝ ጊዜ ሁሉ
እግዚአብሔርን ጠራሁት፤
ስቅስቅ እያልኩኝ በእንባ
የሆዴን ብሶት ነገርኩት፤
ከዚያም በበቀል ወረደ
ከሰማይ አንጐደጐደ፤
በመብረቁ አወካቸው
በፍላጻው በተናቸው።
አዝማች. . .

Song 1-10

I Will Call on God

CHORUS:
I will call on God who deserves praise.
And I will be saved from my enemies.
I will call on God who deserves praise.

1. When the flood of cruelty makes me scared,
And when the agony of hell encircles me,
When he asks me where my God is,
When my enemy scoffs at me,
When he scares me saying "Just wait"
I will call on the name of the Lord.
And I will be saved from my enemy.

2. The name of the Lord Jesus for me
Is a strong wall.
Until this day whoever called on Him
Has not been embarrassed.
Because the One who lives in the cherubim
Gave me full hope,
I will in faith call upon His name,
And I will be saved from my enemy.

3. Whenever I am troubled
I call upon God.
Crying bitterly and brokenly in tears
I told Him the problems of my heart
Then he descended in vengeance;
He came thundering down from heaven
He disturbed them with His lightening
He dispersed them with His arrows.

4. ለጥርሶቻቸው ንክሻ አላደረገኝምና፤
ከተዘረጋብኝ ወጥመድ ሁሉ አድኖኛልና፤
አርነቱን ከሚቀማ ከሰይጣን ጋርዶኛልና
ስሙ ይክበር ሃሌሉያ
እያልኩኝ ልነር በአርሰ ጉያ።

አዝማች . . .(2x)

I-11

እግዚአብሔር ኃያል

እግዚአብሔር ኃያል ፤
በሰልፍም ደግሞ ኃያል፤
ክቡ አስክ ዛሬ
ለማን ተረቶ ያውቃል?
} አዝ. (2x)

1. ሕዝቡን ክልሉ የሚዋጋ
ለጠላት ዛቻ የማይሰጋ፤
ብድራትን መላሽ የኛ አምላክ፤
ይርታ እንጂ መረታትን አያውቅ፤
ይርታ እንጂ መረታትን አያውቅ።

አዝማች. . .

2. የእምነት ባለ ድል ሳይጸጸት፤
ጌታውን አምኖ ሳያፍርበት፤
ለተስፋው ለብሶ ሰንሰለት፤
ሕይወቱን ሰጥቷል ሳይሰስት፤
ሕይወቱን ሰጥቷል ሳይሰስት።

አዝማች . . .

3. አንተም በኃይሉ ድል ነስተህ፤
በእቶን ተፈትነህ ነጥረህ፤
ለመንግሥቱ ብቁ ሆነህ
እንድትወጣ ጌታ ይርዳህ፤
እንድትወጣ ጌታ ይርዳህ።

አዝማች . . .

4. ያን ጊዜ ተዋግቶ የረታ፤
የጠላቱን ጅማት የፈታ፤
በጽኑ አመታት የሚመታ፤
ሁሉንም የሚችል የድል ጌታ፤
ሁሉንም የሚችል የድል ጌታ። /አዝማች.../

4. He did not put me into the clamp of their teeth
He always saved me from the trap which was set for me.
He protected me from Satan
Who would snatch away my freedom.
Praise be to His name, Hallelujah
May I live in His bosom/the secret place.

Song 1-11

God Is Mighty

CHORUS:

God is mighty.
He is mighty in battle, too.
By whom was He ever defeated?

1. Protecting His people, He fights;
He is not fearful of the enemies boasting.
He is the One, our God, who takes revenge;
He defeats but never has been defeated. (2)

2. The victorious in faith, without any regret
Believing in the Lord, without feeling ashamed of Him,
Wearing chains for His hope,
He gave away his life unreservedly. (2)

3. You, too may win in His power.
Being tested and purified in/by the furnace
You will be fit for His kingdom.
May the Lord help you. (2)

4. The one who fought and defeated,
Who loosened his enemy's tendon
Who strikes a hard hit.
The omnipotent, victorious Lord. (2)

I-12

የማይናወጥ መሠረቴ

የማይናወጥ መሠረቴ፣
ጌታ ኢየሱስ መከታዬ፣
የሕመሜ ፈውስ መድኃኒቴ።
} አዘ.

1. በዚያ በሸለቆ በአዝቅቱ ቦታ፣
የሱስ አልተውከኝም እንዲያ ስንገላታ፣
ሕይወቱ ነህና ተድላ መከታዬ፣
የሱስ ያንተ ፍቅር የቱ ነው ጋሻዬ።
አዝማች . . .

2. የዓለሙ ወጀብ ሊመታኝ ሲቃጣ፣
ጌታ አለቀቀኝም ከእጁ እንድወጣ
ወደ እሱ የመጡትን ልጆቹን ያፈቅራል፣
በእቅፉ ውስጥ ይዞ ይጠበቃቸዋል።
አዝማች. . .

3. የጣርህን መጠን በምን ልገምተው?
የውለታህን ልክ በምን ላስተውለው?
ከቶ እንዳልዘነጋው ያንን መስቀልህን
ደግሞም እንዳልረሳው ለእኔ ማንላትህን።
አዝማች. . .
ጌታ ኢየሱስ መከታዬ
የሕመሜ ፈውስ መድኃኒቴ፣
የሕመሜ ፈውስ መድኃኒቴ፣
መድኃኒቴ፣ መድኃኒቴ።

Song 1-12

My Unshakable Foundation

CHORUS:

My unshakable foundation,
Lord Jesus, my protection
Healer of my pains, my Savior.

1. That valley, the place where I was sad -
Jesus, You did not leave me there lest I wander.
You are my life, my joy and my protection,
Jesus, Your love is my shield.

2. When the world's storm tends to beat me
Lord, did not let me go out of His hand.
The Lord loves His children
And, holding them in His bosom, He will watch them.

3. How can I estimate the amount of Your suffering?
And how can I understand the extent of Your favor?
May I never forget Your coming for me
The healer of my sickness and my savior.

I-13

እታገላለሁ

እታገላለሁ፣ እታገላለሁ፣
እስከ መጨረሻው እታገላለሁ፤
የእስራኤል አምላክ
ድል እንደሚሰጠኝ አምናለሁ።። } አዝ.

1. ጉልቤቴን አጠንክሬ
ክንዶቼን አበርትቼ፣
እጓዛለሁ በደስታ
ሳይከፋኝ ተጽናንቼ።።
አዝማች . . .

2. የሰላምንም ወንጌል
በእገሬ ተጫምቼ፣
በክንፉ ተማምኜ፣
በደሙም ተሸፍኜ።።
አዝማች . . .

3. ፍላጻ የማይበሳውን
ጥሩሩን አሰብሳለሁ፣
ሕይወቴን ሳላስደፍር
በተጠንቀቅ እቆማለሁ።።
አዝማች. . .

4. እምነት ጋሻቸው ሆኖ
ቅዱሳን ከተጓዙ፣
ኑሮአቸው ከተቃና
ድልን ከተቀዳጁ።።
አዝማች. . .

5. በመታገል ከሆነ
ማሸነፍ ድል መንሣት፣
ከዚህ ዓለም ገሸር ጋራ
ከክፉትም ሠራዊት።።
አዝማች. . .

6. የተዘጋጀልኝን ከየሱስ ከጌታዬ
እወስዳለሁ አክሊሌን በሚገባ ታግዬ።።
እታገላለሁ እታገላለሁ
እስከ መጨረሻው እታገላለሁ፤
የእስራኤል አምላክ
ድልን እንደሚሰጠኝ አምናለሁ።። } አዝ. (2x)

Song 1-13

I Will Struggle

CHORUS:

I will struggle, I will struggle
I will struggle until the end.
I believe the God of Israel
Will give me victory.

1. Strengthening my power
And my arms strengthened,
I will travel along happily
Not depressed, but encouraged.

2. Putting on my feet
The gospel of peace
Trusting in His shelter
And covered by His blood.

3. I will put on the breastplate
Which arrows cannot penetrate.
I will not let my life be intimidated.
I will stand alert.

4. If the saints travel
Making faith their shield
If their lives go well
And they gain the victory,

5. If defeat and triumph
Is gained by being patient,
Over the rule of this world
And over the evil army.

6. All that which has been
Prepared for me by Jesus my Lord,
I will receive – and my crown
After I fight well.

1-14

እምቢ አሻፈረኝ

እምቢ አሻፈረኝ
ለምስሉ አልሰግድም፤
ለሰው እጅ ሥራ አልንበረከክም፤ } አዝ.
ከናቡከደነጾር የቁጣ ነበልባል
የማመልከው ጌታዬ በርግጥ ያድነኛል።

1. የሙታን ባልንጀራ
ኃጢአተኛ ሳለሁ፤
ጌታን በማመኔ ከጥፋት ድኛለሁ።
የሕይወቴን ጌታ እንድክድ
አሁን ብገደደም፤
ኢየሱሴን ክጄ
ግዑዝ አላመልክም።
አዝማች. . .

2. እቶኑ ይታየኛል
ግለቱ ይሰማኛል፤
በእጄ አልጠላውም
አንጽቶ ያጠራኛል፤
ለሰማያዊው መንግሥት ብቁ ያደርገኛል፤
ሰው እንደሚያስበው መቼ ይጉዳኛል።
አዝማች. . .

3. በእሳት ውስጥ ያሉትን
ጭስ ላይነካቸው፤
አስረው የጣልዋቸውን
ወላፈን ፈጃቸው ፤
እንደዚህ የሚሠራ
ኃያል ጌታ ካለኝ፤
ለባት አጥፍ ያንድድ
እኔ ምን ቸረገኝ።
እምቢ አሻፈረኝ
ለምስለ አልሰግድም፤
ለሰው እጅ ሥራ አልንበረከክም፤
ከናቡደነጾር የቁጣ ነበልባል
የማመልከው ጌታዬ በርግጥ ያድነኛል።
እንቢ፤ እንቢ፤ እንቢ።

Song 1-14

I Refuse, I Refrain

CHORUS:

I refuse, I refrain.
I will not worship the image.
I will not kneel down before a man-made thing.
From the burning anger of Nebuchadnezzar,
My Lord, whom I serve, will certainly deliver me.

1. A friend of the dead
A sinner was I
Believing the Lord, I was saved from loss.
Though I'm forced to deny now
This life of mine.
I will not deny my Jesus
And worship an idol.

2. I can see the furnace.
I can feel the heat.
I'll not hate it because of fear
It will purge and cleanse me
It will make me fit for His heavenly kingdom
It would never bring hurt to me as people might think.

3. Those who were in the fire
Even the smoke hasn't affected them.
But to those who tied them up and cast them into the fire
The flame of the fire consumed them.
Since I have such a powerful Lord
Let the fire burn seven times hotter.
What does it matter to me?

ካሴት ቁጥር 2

ሕይወት ለተጠሙት
የምስራች በሉ

II-1

ሕይወት ለተጠሙት የምስራች በሉ፣
እንዲህ ያለ ኑሮ ወደው ቢቀበሉ፣
ኢየሱስ ያድናል፣ ዛሬም ይሰበካል፣
የሚያረካ ምንጭ ለሁሉም ተከፍቷል።። } አዝ..

1. ወንድሞች በኅብረት ቢቀመጡ ቀርበው፣
ለማነጽ የሚጠቅም የጸጋ ቃል ይዘው፣
አፋቸውን ሲከፈቱ በክርስቲያን ቋንቋ፣
ምንኛ ደስ ይላል ሲቀር አሉባልታ።።
አዝማች . . .

2. የመንፈስን ፍሬ አዝሉ በሕይወቱ፣
የእምላክ እንደራሴ ታውቆ ማንነቱ፣
ጌታን ሲያንጸባርቅ እስከ ዕለተ ሞቱ፣
ከክብር ወደ ክብር ይለወጣል ፊቱ።።
አዝማች. . .

3. ሸክሙን ለማራገፍ በመስቀሉ እግር፣
ክርስቲያን ሲንበረከክ ልቡ ሲሰባበር፣
ምሥጢሩን ለጌታ በእንባ አዋይቶ፣
ተጽናንቶ ይነሣል፣ በእምነት ተሞልቶ።።
አዝማች. . .

4. ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረቱ ጠንክሮ፣
ሕይወት ሲስተካከል ግንኙነት ሰምሮ፣
ኑሮ ከኢየሱስ ጋር ዓለምን ያስንቃል፣
ለዛ አለው፣ ይጥማል፣ ቢመረጥ ይበጃል።።

CASSETTE 2
ENGLISH TRANSLATION

Song 2-1

Tell the Good Tidings

CHORUS:

Tell the good tidings to those who thirst for life.
If they gratefully accept such a life,
Jesus saves. He is preached even this day.
A satisfying fountain is flowing for all.

1. If brothers in fellowship would sit closer
Having the Word of Grace useful for edification
If they would open their mouths in a Christian language
What a joy it would be when gossip would be absent.

2. Bearing the fruits of the Spirit in his life
The ambassador of God is identified.
If he reflects the Lord till the day of his death,
From glory to glory shall his face be changed.

3. To unload his burden at the foot of the cross
When a Christian kneels down with a broken heart
Telling his secrets to the Lord in tears,
He will rise comforted, filled with faith.

4. Strengthening fellowship with God
When life is made straight by successful relationships
Life with Jesus is preferred to the world;
It has a flavor, is tasty; it is worth choosing.

I-2

አስብበት ዛሬ

አስብበት ዛሬ፣ ነገን አትጠብቅ
ራስህን ስትደልል ዘመንህም አይሰቅ፣
ሕይወት ኢየሱስ ነው፣ ሌላስ አታግኝም፣
አምነህ ድነኅበት ታተም ለዘላለም።

አዝ

1. የጸጋ የምሕረት ዘመኑ አብቅቶ፣
ብርሃን ተሰውሮ የጥሪው ቀን መሸቶ፣
ሰማያት ተፈትተው ምድር ስትናወጥ፣
በክልባል አሳት ጌታም ሳይገለጥ።
አዝማች. . .

2. «አብሮ ደስ ይበለን ትንሽ ቆይ ስትልህ፣»
ዓለም በለዘብታ እያባበለችህ፣
ተድላው ትካዜና ቁጭትን ተክቶ፣
ሲያል እንዳትገባ ሳታስበው ከቶ።
አዝማች . . .

3. የእግዚአብሔር ነገር ለፍጥረታዊው ሰው፣
ሊገባው አይችልም፣ ፍጹም ሞኝነት ነው፣
ፍጥረታዊውን ሥጋ መንፈሱ ሲሻረው፣
ያኔ ትረዳለህ መንገዱ ጥበብ ነው።
አዝማች . . .

4. በመንታ መንገድ ላይ ሆነህ ስታማርጥ፣
ፊጽሞ ላትረካ መንገድ ስትለዋውጥ፣
ሞት ጥላውን ጥሎ አፍኖ ላይወስድህ፣
ጌታን ተቀበለው እርሱ ነው የሚያረካህ።
አዝማች. . .

Song 2-2

Think About It Today

CHORUS:

Think about it today; don't wait till tomorrow.
Do not let your years go by in deceiving yourself.
Jesus is life. You won't find someone else.
Believing, be saved and sealed forever more.

1. Before the time of grace and mercy is over
The light having disappeared, the day of invitation darkened,
Before heaven lets loose, the earth will tremble,
Before the Lord appears with the flame of fire,

2. "Let's rejoice together, just wait a moment"
The world says to you deceivingly
The joy replaced by distress and sorrow
Don't enter into Sheol unexpectedly.

3. God's way for the natural man
Is sheer foolishness. He can't understand it.
When the spirit is released from the natural body
You'll understand then. His way is wisdom.

4. While you hesitate to choose – standing at a fork in the road,
While you change roads with no satisfaction,
Before death casts its shadow and takes you blindfolded,
Accept the Lord for He is the One who will satisfy you.

II-3

ጌታ ኢየሱስ፣ አትተወኝ

ጌታ ኢየሱስ፣ አትተወኝ፣
አምላኬ ሆይ፣ አትልቀቀኝ፤
በጭንቀት ታጥሬ እያለሁ፣
ዝም አትበለኝ፣
መጥተህ አውጣኝ።።
} አዝ.

1. ኃጢአት በዛብኝ፣ ጉልበቴም ደከመ፤
መራመድ አልቻልኩም፣ መንገዴም ጨለመ፤
ጠላቴም ይህንን ሲያይ፣ ሊሰብረኝ አሰመ።።

2. አንተን እያሳዘንኩ፣ ደምህን እየረገጥኩ፣
ለልጆችህ ደግሞ እንቅፋት እየሆንኩ፣
መላው ጠፋኝ ጌታ፣ ግራ ተጋባሁኝ።።
አዝማች. . .

3. ቃልህን እንዳላነብ፣ ፍላጐቴ ከድቶኝ፣
ደግሞም እንዳልጸልይ ድካም ተጫጭኖኝ፣
በጣሙን ዝያለሁ፣ ተጐሳቁያለሁ።።
አዝማች. . .

4. በቅዱስ መንፈስህ ሕይወቴ ታትሞ፣
በልጆችህ መሐል የኔ መኖር ጠቅሞ፣
ልገናኝህ አብቃኝ ሁሉ ተፈጽሞ።።
አዝማች. . .

5. መውደቅ በጥቂቱ፣ መሞት በጥቂቱ፣
መሆኑን አይቻለሁ፤ ከመውደቅ ጠብቀኝ
ማዕበሉ እንዳይጥለኝ፣ ጉርፉም እንዳይወስደኝ።።
አዝማች. . .

Song 2-3

Lord Jesus, Do Not Leave Me

CHORUS:

Lord Jesus, do not leave me.
Oh, my God, do not let me go.
While I am tied down in distress.
Do not ignore me; come, pull me out.

1. Sin was too much with me and my strength was weakened.
I couldn't walk and my way was darkened.
My enemy, knowing, dreamed of breaking me.

2. Causing You to be sad, stamping on Your blood
And being an obstacle to Your children,
I am perplexed, I am confused.

3. I lost a desire to read Your word
And I felt drowsy to pray.
I am very exhausted, I am wretched.

4. My life being sealed by Your Holy Spirit
My presence being beneficial among Your children
Qualify me to meet You after all is completed.

5. Falling and dying is caused by small things
For I have realize this, keep me from falling
Lest the storm throw me down and the flood carries me away.

II-4

እንዲህ አልነበርኩም

እንዲህ አልነበርኩም
ዛሬ ግን ሆኛለሁ፣
ያን መልካሙን ሕይወት
የድሮውን ፈልጌአለሁ።

አዝ. (2x)

1. ስምህን እንደ ዋዛ ተሸክሜዋለሁ፣
ክርስቲያን ተብዬም ይኸው እጠራለሁ፤
ውስጤ ቢመረመር ግን እንዲህ አይደለም፣
የመንፈስህ ፍሬ ከቶ በእኔ የለም።
አዝማች. . .

2. የለየልኝም ከሐዲ አልሆንኩኝም፣
ክርስቲያንም ሆኜ ወይ አልበረታሁም፤
እንዲያው ለብ ብዬ አስቸግራለሁኝ፣
ዛሬስ በንስሐ ተደፍቼለሁኝ።
አዝማች. . .

3. ለክርስቲያኖች፣ ለእንተ ያለኝ ፍቅር፣
ሳገለግልህም ስምህን ሳስከብር፤
የነበረኝ ጸሎት ያ ሁሉ ትጋቴ
እፍገመገማለሁ ከድቶኛል ብርታቴ።
አዝማች. . .

4. ሽቅብ እንደ መውጣት፣ ቁልቁለት ሄጃለሁ፤
ወደ ሞትም ደጃፍ በጣም ቀርቤአለሁ፣
አሁንም በቃልህ ተገሥጬአለሁኝ፣
ዳግም አንሣኝ ብዬ ተማጽኛለሁኝ።
አዝማች . . .

Song 2-4

I Was Not Like This

CHORUS:

I wasn't like this but today I am
I'm desiring the previous better life.

1. I have carried Your name as a simple thing
And yet I am called a Christian.
But if inside me were to be examined, this isn't true.
The fruit of the Spirit is not in me at all.

2. I haven't become a true atheist.
Nor am I strong as a Christian.
In fact, being lukewarm, I am in a dilemma.
But today in repentance, I prostrate myself.

3. The love I had for the Christians and You
When I served You, glorifying Your name
The steadfastness of prayer I had -
All declined and I'm trembling in weakness.

4. Instead of climbing up, down I went.
I am very near to the gate of death
Now I am rebuked by Your word.
I have appealed to You to raise me up again.

II-5

በጭንቱቴ ተጨንቆ መስቀል ላይ ተሰቅሎ

በጭንቱ ተጨንቆ፣ መስቀል
ላይ ተሰቅሎ፣
ላልረባሁት ልጁ እንዲያ ተጉሳቁሎ፣ } አዝ.
ደሙን አፈሰሰ፣ በፍቅሩ ተገደ፣
ሕይወቴን አዳናት፣ ስለ እኔ ተዋርዶ። (2x)

1. የሠራዊት ጌታ፣ ኃያሉ መድሀኔ፣
ሲጠብቀኝ ሳለ ፍርድና ኩነኔ፣
በኃጢአት ሐረግ ስናር ተሳስሬ፣
ከእስራቴ ፈታኝ፣ መራኝ ወደ ሀገሬ። (2x)
አዝማች. . .

2. ፍጹም የማልረባ፣ ማስተዋል የሌለኝ፣
አዳኜን የማላውቅ፣ ፍርድ የሚጠብቀኝ፣
የሰይጣን ምርኮኛ፣ ሸክም የተጫነኝ፣
እንዲህ ያለሁ ነበርኩ ጌታ ሳያገኘኝ። (2x)
አዝማች. . .

3. ፍርሃት መጠራጠር፣ ክፋትና ርኩሰት፣
ይወገድ ትዕቢት፣ ቅንዓት ምቀኝነት፣
ተንኮልና ውሸት፣ ሐሜት ክፉ ምኞት፣
ተደምስሰው ይጥፉ በጽዮኑ ዓለት። (2x)
አዝማች. . .

4. ይውደቁ፣ ይፈጩ፣ ይድቀቁ በአንድነት፣
ቀንበሩ ተሰብሯል፣ ይቅርብኝ ባርነት፣
ዕዳዬም ተከፍሉ፣ ታውጇል አርነት፣
ሞትም አያስፈራኝ፣ ተሰጥቶኛል ሕይወት።
(2x)

Song 2-5

Hanging on the Cross

CHORUS:

Hanging on the cross, by my distress He was distressed.
He was afflicted like that for His wretched son
Compelled by His love, He shed his blood.
Humiliated on behalf of me, He saved my life. (2x)

1. Lord of hosts, my powerful Savior,
When judgment and damnation awaited me,
When I was crying in sin, living bound,
He untied me from my binding and led me to my country. (2x)

2. Completely useless and dull was I,
One who knew not his Savior, awaiting judgment,
A captive of Satan and pressed by his load,
I was such a person before the Lord found me. (2x)

3. Let fear, doubt, evil and uncleanness,
Jealousy and envy be eliminated from now on.
Mischief, lies, gossip, evil wishes –
Let them be destroyed by the rock of Zion! (2x)

4. Let them altogether fall, be ground down, changed to powder.
The yoke is broken; I want no more slavery.
My debt being paid, freedom is proclaimed.
Death does not frighten me. Life is given to me. (2x)

II-6

በአምላክ አምሳል

1. በአምላክ አምሳል ተፈጥሬ፣
   በጐ ለማድረግ በፊቱ፣
   ስናር ሳለሁ ኃጢአቴ፣
   አድርጐኝ ነበር ከንቱ፣
   ክቡር ሆኜ ሳለሁ፣ አምላኬን ረስቼ፣
   እንደሚጠፉ እንስሶች መሰልኩ።

2. እኔ ሳልፈልገው ጌታ
   ሊፈልገኝ ከላይ መጥቶ፣
   ከእርኩሰት ውስጥ ነጥቆ አወጣኝ፣
   በዓለም ላይ ተንከራቶ፣
   ሸክሜን ወሰደልኝ፣ በሥቃይ ሞተልኝ፣
   የማይቈጠረውን በደሌን ፋቀልኝ።

3. መድኃኒቴ ነው ኢየሱሴ፣
   ጌታዬና አምላኬ፣
   ስለ መልካሙ ውለታው፣
   ላመሰግነው ተንበርክኬ፣
   ምሕረቱ ብዙ ነው፣
   ማዳኑ ግሩም ነው፣
   ለአምላካዊ ፍቅሩ መጨረሻ የለው።

4. በሞት ጥላ ውስጥ እያለሁ፣
   በድቅድቅ ጨለማ፣
   ኢየሱስ ብርሃኔ መጥቶ
   አዳነኝ መሐሪ ነውና፣
   ለፍርድ የተመደብኩ፣
   ለሲዖል የታጨሁ፣
   የቁጣ ልጅ ስሆን ከፍጥረቴ፣ } አዝ. (2x)
   ቅጣቴን ወስዶ ያ ረድኤቴ።

Song 2-6

I Was Created in God's Likeness

1. I was created in God's likeness.
   To do good in his presence, but
   When I was living in sin, it almost made me useless.
   Losing my dignity I forgot my God
   And I became like the animals that perish.

2. Though I didn't see the Lord
   From above he came to find me.
   He snatched and pulled me out from uncleanness.
   Wretched He was in the world, yet He took my burden.
   He died for me, wiped away my countless errors.

3. He is my Jesus, my Savior, My Lord, my God.
   For His kindness may I kneel and praise Him.
   His mercy is plenteous, His salvation wonderful.
   The love of God has no end.

4. While I was in the shadow of death in absolute darkness
   Jesus my light came. He saved me for He is merciful.
   I was given to judgment, engaged to Sheol.
   While I was naturally a child of wrath
   He took my faults, Jesus my help.
   (Repeat).

II-8

እንዘምራለን

ዘምሩ፣ ለእግዚአችን፣ ዘምሩ፣
ዘምሩ፣ ለንጉሣችን፣ ዘምሩ፣
እግዚአብሔር በምድር ሁሉ፣
ንጉሥ ነውና
በማስተዋል ዘምሩ።። } እዝ.

1. እንዘምራለን፣ እንዘምራለን፣
በጊዜውም፣ ለጊዜውም፣
በሕይወታችን ዘመን ሁሉ፣
ጌታን እናከብራለን።።
እዝማች. . .

2. እንዘምራለን፣ እንዘምራለን፣
በጊዜውም፣ ለጊዜውም፣
በሕይወታችን ዘመን ሁሉ
ጌታን እናከብራለን } 2x
ጌታን እናከብራለን።። 2x

Song 2-8

Sing for Our God

CHORUS:

Sing for our God. .
Sing, sing for our King
For God is the King of all the earth,
Sing to Him with understanding.

We will sing, we will sing
In season and out of season
The whole of our life, we will glorify the Lord (2x)
We will glorify the Lord. (2x)

II-9

ተመስገን ጌታዬ

ተመስገን ጌታዬ፣
ክብር ገናንነት ለስምህ ይሁን።
ተመስገን ኢየሱስ ሆይ፣
ክብር ገናንነት ለስምህ ይሁን።
አዝ. (2x)

1. በግለት እንዲቆይ ላይደክም ጉልበቴ፣
ኃይልን አስታጠቅኸኝ ከላይ መድኃኒቴ።
በብዙ ውሽንፍር ቢያጥለቀልቅ ጉርፉ፣
ጠላቶች በእንተ ስም ሁሉም ተሸነፉ።

አዝማች. . .

2. የኑሮዬ ተገን ክብሬ መከታዬ፣
ኃይሌም ይታደሳል አንተ ነህ ተድላዬ።
ማዕበሉ ተነሥቶ ሊያሰጥመኝ ሲቃጣ፣
በገሐድ አያለሁ ረዳቴ ስትመጣ።

አዝማች. . .

3. የእግዚአብሔር ቸርነት አያልቅም ቢቆጠር፣
ነነዌም ብትሠራ ኃጢአት በማዘውተር።
አምላክም አስቦ እነርሱን ለመምከር፣
አዘዘው ዮናስን ለሕዝቡ እንዲናገር።

አዝማች. . .

Song 2-9
Be Praised, My Lord

CHORUS
Be praised, my Lord.
Honor and fame be to Your name. (4)

1. That I may stay warm without getting weak
You girded me with Your strength from above, my Savior.
Though the strong stormy rain over-flowed in flood,
All the enemies are defeated in Your name.

2. Shelter of my life, my honor, my shield,
My strength will be renewed, You are my joy.
When the storm rises attempting to drown me,
I can clearly see my helper's arrival.

3. The extent of God's kindness cannot be estimated.
Though "Nineveh" does sin frequently.
God, wanting to advise them,
He ordered Jonah to talk to them.

II-10

ላመሰግንህ ዛሬ

ላመሰግንህ ዛሬም የኔ ጌታ፣
ስለማይነገር ስጦታህ፣
ስለማይቆጠር ውለታህ፣
በእውነት አንተ ታማኝ ነህ።
ዘላለም ይወደስ ይክበር ታላቅ ስምህ።

አዝ

1. ትንፋሼንና መንገዴን ሁሉ በእጅህ ይዘህ፣
እንደ ዓይንህ ብሌን አድርግልኝ ተጠንቅቀህ።
ከሚጐዳኝ ነገር ዘወትር ቃልህን ሰውረህ፣
ተመስገን ከማለት ሌላ ላንተ ምን ልክፈልህ።

አዝማች. . .

2. በጎዘን ስመታ ሲከፋኝም አንዳንድ ጊዜ፣
ከብዶ ሲጫጫነኝ ሲደራረብብኝ ትካዜ፣
የመጽናናት ጌታ ማን እንዳንተ ደረሰልኝ፣
የልቤን ተካፍሎ አይዞህ ሊለኝ ሊያበረታኝ?

አዝማች. . .

3. ራሴን አውቀዋለሁ እጅግ አስቀያሚ ነበርኩ፣
ምስኪን ዓላማ ቢስ በኃጢአት የተቅበዘበዝኩ፣
ግን እንዲያው ወደኸኝ ሰው ሆኛለሁ በአንተ
ብርታት፣
በቂ ቃል የለኝም ልገልጽ የውለታህን ብዛት።

አዝማች . . .

4. አሕዛብ ባያውቁህም፣
የኔ ነፍስ ግን ታውቅሃለች፣
የፍቅር ፊትህን በየለቱ ትናፍቃለች።
ያለ አባትነትህ መኖር ከቶ አይሆንላትም፣
መሳይ አጭበርባሪው ሁሉ ከአንተ
አይነጥላትም።

አዝማች. . . (2 ጊዜ)

Song 2-10

Let Me Thank You Today

CHORUS:

Let me thank You today, my Lord,
For Your unspeakable gift
For Your countless favors
You are faithful truly.
May Your great name be praised and glorified forever.

1. Holding all my breath and my ways in Your hand,
Taking care of me like the pupils of Your own eyes,
You have hidden and veiled me from that which could harm me.
What can I pay You except to say thank-you?

2. When I am hit by sorrow and am sometimes sad,
When I am oppressed and depression is added on top of it,
Lord of comfort, who ever came just in time for me but You
To share my burden and to encourage me?

3. I know myself that I was so ugly
I was poor, aimless and restless in sin.
But You took me as I was, and I am made somebody because of You.
I have no words to explain Your numerous kind deeds.

4. Gentiles don't know You, but my soul does.
It daily longs for Your face of love.
And I cannot live without Your fatherhood.
All imitators, deceivers, can't separate my soul from You.

II-11
የእኔ ጌታ

አዝ. የእኔ ጌታ ስለ እኔ ገዶት፤
ኃጢአቴም አስጨንቆት።
ዝም ብሎ እንደ ጠቦት፤
በሐሰት ተመስክሮበት በችሎት፤
ዕዳዬን ከፍሎታል ተሰቅሎ በመሞት።

1. ጌታ ኢየሱስ የእኔ ቤዛ፤
ጉስቁልናዬ ቢበዛ።
ከክብሩ ተዋረደልኝ፤
በእኔ ፈንታ ታረደልኝ።(2x)

2. ግብዝ ያይደለ እንደ ሰው፤
ወረት ጨርሶ ያልነካው፤
በጉልጐታ ላይ የታየው፤
እውነትም እርሱ ፍቅር ነው። (2x)
አዝማች. . .

3. ያደቡት ሁሉ ፈርጥጠው፤
ለሰይፍ ለጉመድ አጋፍጠው፤
በዚያን ምሽት አልቦታል፤
ቃትቶ ነፍሴን ታድጓታል።(2x)
አዝማች . . .

4. በግርፍ ጀርባው ተላልጦ፤
ፍቅሩንም በሥቃይ ገልጦ፤
ንጹሕ ደሙን ለእኔ ከፍሎ፤
በቀራንዮ ደርቆ ውሎ። (2x)
አዝማች. . .

5. ይህ ፍቅር በሕይወቴ ገብቶ፤
የደኅንነት ሥራ ሠርቶ፤
ቆሻሻነቴን ቀይሮ፤
አይቻለሁኝ ውብ ኑሮ። (2x)

Song 2-11
My Lord Was Concerned About Me

CHORUS
My Lord was concerned about me
And my sin worried Him.
Being silent, like a lamb,
When false witness was given against Him and was biased,
He paid my debt, crucified to death.

1. Lord Jesus, my Lord, my ransom,
When my wretchedness was great,
He was dishonored for me;
He was slaughtered on my behalf. (2)

2. He is not a hypocrite as we are;
Custom never touched Him;
What was seen at Golgotha
Was truly love. (2)

3. All who accompanied Him fled
Giving Him up to the swords and clubs.
He perspired that night.
Moaning, He rescued my soul. (2)

4. The skin of His back peeled off by whipping,
Expressing His love in pain,
Paying His pure blood for me,
He spent the day drying up on Golgotha. (2)

5. His love, submerging into my life,
Performing the work of salvation,
Changed my filthiness.
I have seen a beautiful life. (2)

II-12

በሰማይ በምድርም ሙሉ ሥልጣን ያለው

በሰማይ በምድርም ሙሉ ሥልጣን
ያለው፤
የሚለውጥ እንጂ የማይለወጠው፤
አልፋ አሜጋ ማለት ጌታ ኢየሱስ ነው።

አዝ.

1. እግዚአብሔር መንፈስ ነው
በሥጋ የማይጨበጥ፤
እጅግም ታላቅ ነው በለው የማይገመት፤
ዛሬም እንደ ቀድሞው ክንዱ ኃይል
ያደርጋል፤
ቢወዱም ቢጠሉም፤ ኢየሱስ ይነግሣል።
አዝማች. . .

2. ስሙን በመታመን ሲጠሩት ይቀርባል፤
ለደከመች ሕይወት ብርታት ይጨምራል፤
ሞገዱን ፀጥ አርጉ ሰላምን ይሰጣል፤
ምንጩን አጠጥቶ በረሃን ያለማል።
አዝማች. . .

3. የማይታየው ባሕርይ የዘላለም ኃይሉ፤
በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በእውነት ቢያስተ
ውሉ፤
ከጥንትም ጀምሮ ከተሠሩት ደምቆ፤
ይኖራል ኢየሱስ፤ ሕልውናው ታውቆ።
አዝማች. . .

4. የታምራት አምላክ ክንዱ መች አጠረ፤
ሰው ያወቀ መስሎት ብዙ የመረመረ፤
ኃጢአትን አጥጥሞ ለፍርድ እየኖረ፤
«ጌታን የለም» ብሎ እጁን አጣመረ።
አዝማች. . .

Song 2-12

He Who Has All Power

CHORUS

አዝ. He who has all power in heaven and earth
The One who calls, "Come to the Lord,"
Who cannot be changed but who causes change.
The Alpha and Omega is the Lord Jesus

1. God is a spirit and cannot be perceived by flesh.
He is so great and cannot be estimated by men.
Today, like before, He strengthens His arm in power.
Liked or disliked, Jesus will reign

2. He draws near when called by those trusting His name.
He increases strength to the life that is weak
He quietness the storm and gives peace.
He quenches thirst from His springs and turns the desert green.

3. If we could realize it, by the power of the Holy Spirit indeed,
His unseen nature and eternal power
Is revealed beautifully from the very beginning of His creation.
And Jesus lives, making known His existence.

4. The God of miracles, when was His hand ever shortened?
Man, thinking he knew, did a lot of searching.
Loving sin, and living for judgment,
Man folded his hands and said, "The Lord doesn't exist."

II-13

አትጠራጠረው

የሱስን እንደ ሰው አትጠራጠረው፤
መዋሸት አያውቅም፤ ተስፋህን
ጠብቀው፤
አይጥልህምና፤ በመከራህ ጥራው
አፍህ እያመነ፤ በልብህ አትክዳው።። } አዝ.

1. ከጠላት ፍላፃ ከሰይፍ ያድንሃል፤
በረሐብም ዘመን ከሞት ያስጥልሃል፤
ስሙን ያስከብራል፤ ቁም ነገርን ያውቃል፤
ሕፃን ስላይደለ ያለውን ይፈጽማል።።

አዝማች. . .

2. ለታማኝነቱ ተው ገደብ አትስጠው፤
ለወላዋይ ልብህ ጽናት አትንፈገው፤
የዘላለም አምላክ እግዚአብሔር አይዋሽም፤
የገባልህን ቃል ፈጽሞ አይክድም።።
አዝማች. . .

3. ከእርሱ ጋር እስክ ሆንክ ከአንተ ጋራ ነው፤
አውጥቶ እንዳይጥልህ ብቻ አትተወው፤
አሰብ ቆም ብለህ ያሳለፍከውን ዘመን፤
ዛሬም አምነህ ጥራው ያኔ ያዳነህን።።
አዝማች. . .

4. ስሙን እየጠራህ ስንቱን አምልጠሃል?
ከስንቱስ አደጋ ስንት ጊዜ ድነሃል?
ውለታውን ሲረሱ ጌታ ቅር ይለዋል፤
በቃሉ ብታምን ሁሉ ይቻልሃል።።
አዝማች. . .

Song 2-13

Do Not Doubt Jesus

CHORUS:

Don't doubt Jesus as a human being.
He does not know lying, so keep your promise.
He won't forsake you in time of trouble.
Believing with your mouth, don't deny Him in your heart.

1. He will deliver you from the enemy's arrow and sword.
He also will protect you from death in time of famine.
He will make His name honored, and the matter He knows well.
Because He is not an infant, He fulfils what He says.

2. For His faithfulness, don't set limits.
Don't let your doubtful soul hold back in being firm.
The everlasting God does not lie.
What He has promised you He never will deny.

3. As long as you are with Him, He is with you.
Lest He would completely leave you, don't you leave Him.
Stop for a while; think about the days you have wastefully spent.
Even today, believe and call on the One who saved you.

4. As you have called on His name, how many things have you escaped from?
From how many dangers, how many times have you been saved?
The Lord will be disappointed when His favor is forgotten.
But if you believe in His word, all will be possible to you.

II-14

የፍጥረት ገዥ ተቆጣጣሪው

ካፈጠጠብኝ በዓለም ካለው፤
እጅግ ይበልጣል በእኔ ያለው፤ } አዝ.
የፍጥረት ገዥ ተቆጣጣሪው፤
ጌታ ኢየሱስ ከእኔ ጋር ነው።

1. በሰልፉ ሜዳ በዝቶ ጠላቴ፤
ፍርሃት ቢያርደኝ ቀልጦ ጉልበቴ፤
ጠፋሁ ብዬ ስል ወየው ጌታዬ፤
ከፊቴ ያልፋል የሱስ ጋሻዬ።
አዝማች. . .

2 ጠላት እንደ ንብ ተምሞ ቢመጣ፤
ምሽጌን ትቼ እኔም አልወጣ፤
በአግዚአብሔር ስም አሸንፋለሁ፤
ጉልያድን ወድቆ በዓይኔ አያለሁ።
አዝማች. . .

3. ጽኑዕ ኃያሉ የአምላክ ጦረኛ፤
አንዱ ለሺ ነው የእምነት አርበኛ፤
በዐመፀኞች እጅ ደሙን በትኖ፤
ፍሬውን ያበዛል በአምላኩ ታምኖ።
አዝማች. . .

4. ረዳት እንዳለኝ ጠላቴም ያያል፤
እንደ ዘበተ መቼ ይቀራል፤
የመስቀል ጽዋ እኔም እጠጣለሁ፤
ድል ይታወጃል፤ እሻገራለሁ።
አዝማች. . .

Song 2-14

The Ruler and Controller of Nature

CHORUS:
Compared to the one who confronts me in the world,
The One Who is in me is much greater.
The ruler and controller of nature,
The Lord Jesus is with me.

1. If my enemies increase in the battlefield,
If I tremble in fear with melted strength,
When I cry "Woe unto me, Lord, I am lost"
Jesus, my shield, passes in front of me.

2. If my enemy comes like a colony of bees
I will not go out, leaving my fort.
In the name of God I shall win.
I shall see Goliath falling with my own eyes.

3. Firm and strong, warrior of God.
He is one for a thousand, the patriot of faith
Sprinkling his blood at the hands of the sinner,
He multiplies his fruit, trusting in his God.

4. My enemy sees that I have a helper.
He will not continue boasting.
I shall also drink the cup of the cross.
I shall cross over and victory will be proclaimed.

II-15
አየሁ

አየሁ፣ አየሁ፣ አየሁ፣ አሻግሬ አየሁ፣
አምነው የሞቱትን ልመስል ተመኘሁ።። } አዝ.

1. አብርሃምን አየሁ የእግዚአብሔርን ወዳጅ፣
ይስሐቅን ሊሠዋ ለሰይፍ የሚያዘጋጅ፣
ቃሉን ያከበረ ያን ቁም ነገረኛ፣
በአሳቡም ቁርጠኛ፣ የእምነትን አርበኛ።።

ስውር ጣዖት የለውም፣ ከአምላኩ
የሚነጥል።።።
በቀውጢ ዘመናት እምነቱን የሚያስጥል።።

2. ሐዋርያትን አየሁ፣ የጽድቅን ሰልፈኞች፣
የኃጢአትን ጠሮች፣ የእምነትን ቀንደኞች።።
በአንድነት ጸሎት ምድርን ነቀነቋት፣
በድል ብርሃን ወንጌል በአንዴ
አጥለቀለቋት።።

ከጌቶቹ ጌታ ፈቃድ ነበራቸው፣
ሥልጣናት አልቻሉም ዝተው
ሊያግዱዋቸው።።

3. ሰማዕታትን አየሁ እነ አስጢፋኖስን፣
ዓለም ሲጠላቸው አምነው ኢየሱስን፣
የደም ጥማተኞች ፍዳ ሊያሳዩዋቸው፣
ፊታቸው ሲያበራ ያም ሳይበግራቸው።።

ለዓለም ሲያማልዱ ልክ እንደ
ጌታቸው፣
አቤት ሲያስቀና ያ አሟሟታቸው።።

4. ኮብላዮችን አየሁ ክጨለማ ገብተው፣
ሲያልና ሰይጣን ጌታም የለም ብለው፣
በስሙ ዘብተው፣ በደሙ ቀልደው፣
የለም ካሉት ጋራ በሞት ተገናኙተው።።

መንፈሴ አያቸው፣ በአንድነት
ሲንጫጩ፣
በሙታን ዓለም ውስጥ በጣም
ሲወራጩ።።

Song 2-15
I Saw

I saw, I saw, I saw
I saw, over across the way,
Those who died believing.
I coveted to be like them.

1. I saw Abraham, the friend of God
Who prepares the sword
To sacrifice Isaac.
He keeps his word, a nobleman.
He is decisive about his thoughts;
He is a patriot of faith.
He does not have a hidden idol
Which separates him from his God,
Or which, in time of crisis
Snatches his faith.

2. I saw the apostles,
The soldiers of love, the enemies of sin,
The leaders of faith.
By the united prayers they shook the earth,
In victory, in the gospel light
They flooded the world.
They had permission from
The Lord of Lords
Authorities could never stop them with threats.

3. I saw the martyrs such as Stephen.
They believed in Jesus.
The world hated them.
The blood-thirsty
Gave them hardship.
Their faces shone, and they resisted all hardship.
While they interceded for the world
Just as their Master.
Alas. The way they died – makes one to covet it.

5. እንግዲህ ጌታ ሆይ፣ እኔነቴን ግዛ፣
ኪዳኔን እጥፌ ሞትን እንዳልገዛ፣
ብርሃኑ ደብዝዞ፣ ጭጋጉ ሲከበኝ፣
አንተው እየመራህ ወደ ላይ አዝልቀኝ።

የተጻፈው ሁሉ ለትምህርት ሆኖልኝ
በሥርዓት ታግዬ እንዳሸንፍ እርዳኝ።

የተጻፈው ሁሉ ለትምህርት ሆኖልኝ
ገድሉን ተጋድዬ፣ እንዳሸንፍ እርዳኝ።

4. I saw the backsliders entering into the darkness.
They said, Neither hell, Satan or the Lord exist.
They scorned at His name.
They scoffed at His blood.
They met death with those who said He didn't exist.
My spirit saw them all
Making noises together
They were tossing and turning painfully
In the world of the dead.

5. Therefore, my Lord,
Control my being,
That I not forsake my covenant, lest I purchase death.
When the light becomes dim
And when the fog surrounds me,
You lead me and help me to get to the top.
May all that is written be for a lesson.
I'll fight vigorously. You help me to be victorious
May all that is written be for a lesson.
I'll fight the good fight: You help me to be victorious.

ካሴት ቁጥር 3

III-1

እኔ ነኝ ተራራው

እኔ ነኝ ተራራው፤ ትልቁ እንቅፋት፤
የሕዝበህ ጉስቁልና የደካሙ ምክንያት፤ } አዘ.
እ፤ ምንኛ ይመራል የትዕቢቴ ጽዋ፤
ጌታ ሆይ፤ ዝቅ አድርገኝ ሳይገድለኝ ፍሪዋ።

1. የምድረ በዳው ድምፅ አዋጅ ነጋሪው ቃል፤
መንገዱን ጥረጉ አስተካክሉ ያላል።
ኩበሩ ይገለጻል፤
ኮረብታው ዝቅ ይበል፤
ሥጋ ለባሽ ሁሉ እግዚአብሔርን ያያል።
አዘማች. . .

2. ጌታ ትዕቢተኛውን እጅግ ይቃወማል፤
ለትሑታኑ ግን ጸጋውን ያሰጣል።
ለስሙ አገልጋይ ነኝ ዲጋሬ ያንሰኛል፤
የኔ ዝና ወኖቱ፤ ያንተ ተሰውራል።
አዘማች. . .

3. እ፤ ምን ይሻለኛል? ጌታ ሆይ፤ ቶሎ ና፤
ሰምቶ አንተን ለያዩ በእኔ አልቻሉምና።
የልቤን ኮረብታ ተራራውን ናደው፤
ፍሬም እንዳጠፋ ትንሣዔን ግደለው።
አዘማች. . . (2 ጊዜ)

CASSETTE 3
ENGLISH TRANSLATION

Song 3-1

I am the Mountain

CHORUS:
I am the mountain, that great stumbling block.
The cause of wretchedness and weakness of Your people.
Oh, how bitter is the cup of my pride
Oh Lord, make me humble before its fruit kills me.

1. The voice of the wilderness, the word of the spokesman says,
Prepare and sweep the road.
Let the hill be made low.
All human beings shall see God.

2. The Lord greatly opposes the proud
But to the humble He gives His grace.
For formality, I am a servant but I lack Your grace
My prestige shows up but Yours is hidden.

3. Oh, what's the best thing for me? Oh Lord, come quickly
People could not see You through me.
Break the top mountain of my heart
Kill the small seed to multiply the fruit.

III-2

ስብራቴ የማይፈወስ ይመስላል

ስብራቴ የማይወፈስ ይመስላል፤
መድኃኒቴ፤ አንተ ግን ምን
ይለገዛል፤
ምሕረትህ ካለ ማጉረምረም ምን
ይጠቅመኛል?
በእጅህ ውስጥ መውደቅ እ፤ እጅግ
ይሻለኛል።

አዝ.

1. እግሮችም የሉኝም፤ ፊትህ የምቆምበት፤
ዓይኖችም የሉኝም፤ አንተን የማይበት፤
የጠራኸኝ አምላክ፤ ውርደቴን ተመልከት፤
ከጭቃህብት ማጥ አውጣኝ ባንተ ምሕረት።

አዝማች . . .

2. ካንተ የተሰወረ ምን አለ ጌታ ሆይ?
ከቶም ሳይገለጽ ተደብቆ የሚቆይ?
የልቤ መርማሪ፤ የእኔ ውስጥ አዋቂ፤
ቅሌቴን ይቅር በል፤ የነፍሴ ጠባቂ።

አዝማች. . .

3. ምንም ቸር ብትሆን፤ በአንተ አይዘበትም፤
ጉዴን ለመሸፈን ምክንያት አላቀርብም፤
ያው ከነበደሌ ራሴን ሰጥቻለሁ፤
ምረሕ ተቀበለኝ፤ ቃልህን ጥሻለሁ።

አዝማች. . .

4. ምንም እንኳን ዛሬ ሐፍረት ቢሸፍነኝ፤
ፊትህን ለማየት ከቶ ቢያዳግተኝ፤
በተስፋ ዝም ብዬ ቀኔን እጠብቃለሁ፤
በድል ልታድሰኝ እንድትችል አምናለሁ።

አዝማች. . .

Song 3-2

My Brokenness Seems Non–repairable

CHORUS:

My brokenness seems non-repairable
But my Saviour, what is difficult for You?
Since Your mercy is available, what's the use of murmuring?
Oh, it's much better for me to fall into Your hands.

1. I have no feet to stand in Your presence
Nor do I have eyes with which to see You.
Oh God, the One who called me, look at my shame.
Pull me out of the marsh by your mercy.

2. What's hidden from You, Oh Lord?
What remains hidden and not made plain?
You are the examiner of my heart, knower of my interior,
Forgive my scandal, the keeper of my soul.

3. Though You are gracious, You are not to be scorned.
I will not give an excuse to cover up my sin.
With all my transgression, I submit myself to You
Pardon me and accept me. I have violated Your word.

4. Even though today shame covers me
And though it is hard for me to see You face,
I quietly and hopefully wait for Your word;
I believe You can renew me with victory

III-3

ኢየሱስ፣ የነፍሴ መድኃኒት

ኢየሱስ፣ ኢየሱስ፣ የነፍሴ መድኃኒት
የሰላሙ ንጉሥ፣
ኢየሱስ፣ ኢየሱስ፣ ና ሕይወቴን
ፈውስ።።
} አዝ.

1. «ወደ እኔ ጩህ፣ እኔም እመልሳለሁ፣
ታላቁንም ነገር ለአንተ አሳይሃለሁ፣»
በቃልህ ስላልከኝ፣ እንዲህ እጮሃለሁ፣
እንድትፈውሰኝ ስምህን እጠራለሁ።።
አዝማች . . .

2. በድካም ማዕበል ሕይወቴ ተገፍቶ፣
በሚሰብር ብትር ክፉኛ ተመቶ፣
የታመቀው ሥቃይ ልቤን እየጣሰ፣
እንባ አስከትሎ ወደ አንተ ደረሰ።።
አዝማች. . .

3. «አልጥልህም» ብለህ፣ «ከቶም አልለቅህም፣»
የገባህልኝ ቃል አልተዘነጋኝም፣
«እኔ ፈዋሽህ ነኝ» ብለህ የፈወስከኝ፣
ከጉስቁልናዬ ና ዛሬም አድነኝ።።
አዝማች. . .

4. ሰባራውን ጠጋኝ፣ የፈረሰውን አዳሽ፣
ፈዋሼ አንተ ነህ፣ የእምባዬ አባሽ፣
ለምች ያላዩትን ቁስሌን ያየህልኝ፣
አንተ ብቻ እኮ ነህ ዛሬም ያለህልኝ።።
አዝማች . . .

Song 3-3

Jesus, Cure of My Soul

CHORUS:

Jesus, Jesus, cure of my soul, the king of peace,
Jesus, Jesus, come, and cure my life.

1. "Call unto Me and I will answer
And I will show you a great thing."
Because You told me in Your word, I, thus am calling
I am calling Your name that You may cure me.

2. My life pushed around by storms of weakness,
It was badly hit by a hard stick.
The repressed pain, getting an outlet from my heart
And followed by tears, has reached You.

3. You said, "I will not cast you out and I will never leave you."
I have not forgotten what You promised me.
You said, "I am your healer" and You healed me.
Come and save me today from my wretchedness.

4. Fixer of the broken, repairer of the torn down,
You are my healer, and You wipe my tears away.
You saw my wounds which other people could not see.
Of course, You are the only one Whom I have today.

III-4

ጠላቴ ሆይ፣ ብወድቅ እነሣለሁኝ

ጠላቴ ሆይ፣ ብውድቅ እነሣለሁኝ፣
በጨለማ ብቀመጥ እንኳን
እግዚአብሔር ብርሃን ይሆንልኛል፣
ስለዚህ፣ ስለዚህ፣ በኔ ደስ አይበልህ።

አዝ.

1. የወይኑ ፍሬ ተሰቅሞ እንደ ቀረው ቃርሚያ፣
ደርቄ ቆሜያለሁ እኔ ከበረከትህ በስተያ፣
የሐዘን እንጉርጉሮዬን የምሬት ለቅሶዬን፣
በአምላኬ ፊት አለቃለሁ እንዲያይት ሕይወቴን።

አዝማች. . .

2. በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአትን
ሠርቼአለሁና፣
ቁጣው ለቅጣቴ ሆኖ ነዶብኛልና፣
ወደ ብርሃን እስኪያወጣኝ እታገሣለሁኝ፣
መልሶም እስኪምረኝ ድረስ እጠብቀዋለሁኝ።

አዝማች. . .

3. በኔና ባምላኬ መሐል የሚኖረውን ጉዳይ፣
ኢየሱስ ይፈጽመዋል የመሠረቱ ድንጋይ፣
ስለዚህ፣ ጠላቴ ወግድ፣ ጌታ ይገሥጽህ፣
አሁንም ቢሆን ልጁ ነኝ፣ ተረዳ ከልብህ።

አዝማች. . .

4. ለዘላለም አይቆጣም፣ ምሕረትን ይወዳል፣
የጠላቴን ምኞት ቆርጦ አልልታውን
ያቆማል፣
የውርደት ማቄ ተቀዶ፣ ነጭ ልብስ ለብሼ፣
ዳግም አዘምራለሁ ለአርሱ፣ ክንዱን ተንተ
ርሼ።

አዝማች. . .

Song 3-4

O, My, Enemy, If I Fall,

CHORUS:

O, my enemy, if I fall, I will also rise.
Even if I sit in the dark, God becomes my light.
So, so, don't gloat over me.

1. I am like one who gathers summer fruit at the gleaning of the vineyard
I stand dry beyond the blessings.
My lamentation of sorrow, my cry of bitterness
I leave before my God so He can see my life.

2. For I have sinned against God,
His anger fell upon me like thunder for my punishment.
I will be patient until He takes me out to the light.
I will wait for Him until He redeems me.

3. The business between God and me
Will be finalized, completed by Jesus, the cornerstone.
So, my enemy, get away! May the Lord rebuke you.
Even now I am His child. Be clear about that in your heart.

4. He loves forgiveness; He is not angry forever.
He disrupts my enemies' wishes and stops their joy-cries
Tearing off my coarse clothes of disgrace and wearing white garments
I will sing for Him again, leaning on His arm.

III-5

የሠራልኝን ድንቅ ታሪኩን ላውጋችሁ

የሠራልኝን ድንቅ ታሪኩን
ላውጋችሁ፤
ሰዎች እስቲ ስሙ፤ ትምህርት
ይሁናችሁ፤
በጌታ ይታመን፤ ይጽናና ልባችሁ።። } አዝ.

1. በዕለት እርምጃዬ እግሬ ሊያሰስ ቀድሞ፤
ምሕረቱን አብዝቶ ታምራቱን ደግሞ፤
አሳየኝ አምላኬ የከበረ ነገር፤
እንደዚህ ሊመራኝ ወደ ጻድቃን አገር፤
ወደ ጻድቃን አገር።።
አዝማች. . .
2. በቀኝ በግራዬ አድብቶ አድብቶ፤
መልካም መሰል አጥፊ ወጥመዱን ዘርግቶ፤
ጌታ ግን ሲያድነኝ በርሱ ተደራጅቶ፤
ዲያብሎስ ሊያጠቃኝ ነበር ተሰናድቶ፤
ነበር ተሰናድቶ።።
አዝማች. . .
3. እርሱ ቅጥር ሲቀጥር፤ በአምላኬ እየዘለልኩ፤
ወጥመድ ሲዘረጋ፤ እኔም እያመለጥኩ፤
በኔ ብርታት ሳይሆን፤ በጌታ እየታመንኩ፤
ሩጫ እቀጥላለሁ ሁሉን እያሸነፍኩ፤
ሁሉን እያሸነፍኩ።።
አዝማች. . .
4. በዘላለም መድህን ከጥልቁ ወጥቼ፤
ከአባት፤ ከእናት፤ ዘመድ የሚበልጥ አግኝቼ፤
በአሕዛብ መካከል ለእርሱ አዘምራለሁ፤
የከበረ ስሙን አመሰግናለሁ፤ አመሰግናለሁ።።
አዝማች. . .

Song 3-5

Let Me Tell You The Wonderful Story

CHORUS:

Let me tell you the wonderful story of what He's done for me.
You all, please do listen. Let it be a lesson to you.
Let your hearts trust. Be comforted in the Lord.

1. Jesus, walking before me in my daily life
Increases His mercy and His miracles also.
My God showed me a great and noble thing
To lead me like this to the country of the righteous.

2. From my left and right, ambushing and ambushing
Spreading his deceitful and deadly net
But when the Lord saved me by His compassionate love,
The devil was prepared to attack me, was prepared.

3. Jumping over the fence of my enemy
As he spreads the snare, I continue to escape.
Not by my might but by trusting the Lord
I'll continue racing, defeating all, defeating all.

4. By the eternal Saviour, I narrowly escaped.
I found a better friend than father, mother and relatives.
I will sing to Him in the midst of the unbelievers.
I will gave thanks to His honoured name.
I will give thanks.

III-6

መነቀፍን ፈርቶ

አዝ.

መነቀፍን ፈርቶ፣ ማመን አፍሮ፣
ውድ አምላኩን ትቶ፣ ቃል
ኪዳኑን ሰብሮ፣
ኧረ ስንቱ፣ ስንቱ፣ ሰመጠ ባሕር
ገብቶ፣
ጌታ፣ ቶሎ ድረስ፣ እርዳኝ ቢልህ
እጁን ዘርግቶ፣ ተጸጽቶ።።

1. በመንፈስ ጀምሮ ሮጦ፣ ሮጦ፣
ክዓለም ማዕረግ መስቀል መርጦ፣
ዛሬ ግን በወሬ ልቡ ቀልጦ፣
መመካከር ያዘ ጠላት መርጦ።።
አዝማች. . .

2. እርግማን አይደለም መቃሰሉ፣
መነቀፍ ክብር ነው፣አስተውሉ፣
ከአሁኑ ዓለም ተወዳጅቶ፣
ክርስቶስን መተው ይቅር ኮቶ።።
አዝማች. . .

3. መስቀሉን ከጫንቃቸው ሰጣሉ፣
«እኛም ክርስቲያኖች ነን» ለሚሉ፣
ይለፍ ለሌላቸው መንገደኞች፣
እንጸልይላቸው ለከብላዮች።።
አዝማች. . .

4. መስጠሙን ቢረዳ ዓይኑ በርቶ፣
ንስሐ ቢገባ ዳግሞ ከቶ፣
እጅህ መቼ አጠረ የማዳንህ፣
ከጥልቁ ቢጣራ ብኩን ልጅህ?
አዝማች. . .

Song 3-6

Afraid of Criticism

CHORUS:

Afraid of criticism, ashamed of believing,
Deserting his dear God, breaking His promises
Oh, how many, many, got drowned into the sea?
Lord, reach him quickly if he stretches out his hand and says "Help me" in regret.

1. Beginning with the Spirit, he ran and ran
He chose the cross rather than being appointed by the world.
He wasn't appointed to a top-ranking position
But today his heart melted with rumours and began to chat with the enemy.

2. To be belittled is not a curse.
Be assured, it is honourable to be criticized.
By being friends of this present world
Deserting Christ should be completely stopped.

3. For those who dropped off the cross from their shoulders
And for those who say, "We, too, are Christians."
For those travelers who do not have passports
Let us pray for these deserters.

4. If his eyes could open and see that he is drowned
If he could repent and begin to have zeal again
Is Your saving hand short at all
When Your prodigal son calls from the deep?

III-7
ሥጋ ነፍሱን ጠልቶ

ሥጋ ነፍሱን ጠልቶ ዐመጽ አቆጥቁጦ፣
ትሕትና ተረስቶት፣ የትዕቢት ዓይን ፈጦ፣
ፍቅርህን ገደል ከቱ ጥላቻን ለማንገሥ፣
ጥርሱን ይስል ጀመር ሰውን ለመነካከስ፣
አንተ ግን ጌታ ሆይ፣ ምሕረትህን አፍስስ፣
አንተ ግን ጌታ ሆይ፣ ምሕረትህን አፍስስ።

አዝ.

1. በተዘረጋ ክንድ፣ በበረታችም እጅ፣
በጌታ መዳኑን ከሞት ከሲያል ደጅ፣
እንደ ምን ዘንግቶ ሰው ያጉረመርማል፣
ወንድሙን ለመውገር እጁን ይዘረጋል።
አዝማች. . .

2. ስፍራውን ለቆ ሲሄድ፣ ለመጉደል ሲቸኩል፣
ትሕትናውን አውልቆ፣ ለሞት ሲንቀሰቀል፣
እዩት ያንን ዝንጉ ቃል ኪዳኑን ሲያፈርስ፣
በዓመፁው ብዛት ፍቅርን ሲያቀዘቅዝ።
አዝማች. . .

3. አንተን እየፈራሁ ቀኑን ሁሉ ልኑር፣
ትሕትናም አይራቀኝ አልንፈግህ ክብር፣
እጅህ እንዳይመታኝ አጉል ደፋር ሆኜ፣
መተረቻ እንዳልሆን በሐፍረት ተከድኜ።
አዝማች. . .

Song 3-7
Flesh Is Reviving

CHORUS

Flesh is reviving and sin is sprouting
Humility forgotten, the proud eye stared
Throwing love to the cliff to give power to hatred
People began to sharpen their teeth to bite each other.
But You, dear Lord, pour out Your mercy. (2)

1. By stretched out arms and by the strong hands of God
He is saved by the Lord from the gates of death and hell.
How can man forget and start to murmur.
He stretches his hands to stone his brother.

2. Leaving his place, hurrying to failure
Putting off humility, getting restless only to die,
Look at that forgetful man breaking his promises
By the attack that he brought, he froze love.

3. Let me live all my days fearing You.
Lest I lack humility and fail to honour You
Lest Your hand strike me for my rudeness.
Lest I be ridiculed and covered in shame.

III-8
ዘመኑ ፈጠነ

ዘመኑ ፈጠነ፤ ሮጠ ገሰገሰ፤
የጌታችን መምጫ ጊዜያቱ ደረሰ፤
ሰዎች ቶሎ በሉ መከሩን ሰብስቡ፤
የተጣለብንን አደራ አስቡ።

አዝ.

1. ሰዓቱ ሊሞላ በቅርብ ነው ያለ፤
መለከት ሊነፋ በቅርብ ነው ያለ፤
ነገሩ ሊያከትም በቅርብ ነው ያለ፤
ጌታም ከተፍ ሊል በቅርብ ነው ያለ።

አዝማች. . .

2. ሰማያት ሲከብዱ፤ ደመናው ሲጠቁር፤
ምድራችን ስታምጥ፤ ነገር ሲቀያየር፤
ምን አዚም ዞረብን እንዳናይ ጊዜያቱን?
ተዉ፤ ነቃ እንበል እናቁም እንቅልፉን።

አዝማች. . .

3. ሰዉ ሲተራመስ ሞትን ለመሳለም፤
ከአምላክ ተለይቶ በኃጢአት ሲታመም፤
ጠቢብ እንኳን ሲስት፤ በሰይጣን ሲታለል፤
ተነሱ እንናገር፤ ለነፍስ እንታገል።

አዝማች. . .

4. ለራሱ ያልሞተ፤ እራሱን ያልካደ፤
ጌታ የማይገዛው፤ ኃጢአት ያልታገደ፤
በምኑ ይመስክር፤ ልቡ ይንቀጠቀጣል፤
ዋጋም ክፈል ሲባል ከዶ ይፈረጥጣል።

አዝማች. . .

Song 3-8
The Season Speeded

CHORUS:

The season speeded, ran, and hurried on.
The coming of our Lord has approached.
You people, hurry up and gather the harvest.
Think of the responsibility that has been put on us.

1. The time will soon be fulfilled.
The trumpet is to be blown soon.
The matter is to come to an end soon.
The Lord is to appear soon.

2. When the sky gets heavy and the clouds get dark
When our land labours in pain and when things change
Who bewitched us that do not observe the times?
Please, let us be awake and let us not sleep.

3. When people get too busy to salute death
When they get sick in sin because of their departure from God
When even the wise become fools and deceived by Satan,
Let us rise up and speak; let us struggle for souls.

4. One, not dead to himself, denied not himself.
The Lord doesn't control him; he is not restrained from sin.
What helps him to testify? His heart is trembling.
He denies and flees when asked to pay the price.

III-9

ያ ተንከራታቹ

ያ ተንከራታቹ፣ ኮብላይ ወገናችን፣
መጥቷል እንደገና፣ እሰይ ደስ ይበለን፣ } አዝ.
ያ ተንከራታቹ፣ ኮብላይ ወገናችን፣
መጥቷል እንደገና፣ እሰይ ደስ ይበለን:: (2x)

1. በመዳኑ ምክንያት መላእክት ፈንጥዘው፣
በአገልግሎቱ ብዙ ሰዎች ረክተው፣
ታንጸውበት ሳሉ፣ እንቅፋት አግኝቶት፣
ወድቆ የነበረው አዳኙንም ክዶቶት::

አዝማች. . .

2. መርዶውን እየሰሙ ሰዎች አልቅሰውለት፣
ጌታም እንዲያስነሣው ከልብ ጸልየውለት፣
በመራራ ጩኸት ለአምላኩ ነግረውለት፣
መልሶ አምጥቶታል እግዚአብሔር አዝኖለት::

አዝማች. . .

3. የውድቀቱን ምክንያት ነግሮ አስጠንቅቆታል፣
ወንድሞቹን ቀድሞ ጌታ አልቅሶለታል::
ተግሣጽን እየናቀ ከወጥመድ ቢገባም፣
ጌታ ቸር ነውና አልጨከነበትም::

አዝማች. . .

4. ያን ጨካኝ አንበሳ በግልጽ አሳፍሮ፣
በብርቱ በትር መንጋጋውን ሰብሮ፣
ዳግም አምጥቶታል፣ እግዚአብሔር ይመስገን፣
ሙሾው ተለውጧል፣ እሰይ ደስ ይበለን::

አዝማች. . .

Song 3-9

That Wanderer

CHORUS:

That wanderer, deserter, member of ours
Has come again, hurrah, let us rejoice.
That wanderer, deserter, member of ours
Has come again, hurrah, let us rejoice.

1. Because he was saved the angels rejoiced.
And by his service many people were satisfied
When people were edified by him, an obstacle got him
Yes, the one who denied his Savior and fell.

2. People who heard this bad news wept for him.
They prayed from the heart so the Lord might raise him.
By their bitter cry they mediated for him unto God
God has pitied him and brought him back.

3. He told him the reason for his failure and cautioned him
The Lord wept for him even before his brothers did.
Though he enters the trap ignoring reprimand
The Lord is so kind; He has not been harsh with him.

4. Putting that fierce lion to shame publicly
Crash his jaw with His strong rod
Praise God, He has restored him back.
Wailing is changed to joy, hurrah, let's rejoice.

ባስተመጣከኝ ቦታ ጸንቼ እንድቀይህ

ባስተመጣከኝ ቦታ ጸንቼ እንድቀይህ፣
መጥተህ ስትጐበኘኝ በእኔ ደስ
እንዲልህ፣
ጸጋህን አብዛልኝ፣ ጌታ ሆይ፣ አባክህ።
} አዝ.

1. ገነት መኖሪያዬን ሠርተህ ውብ አድርገህ፣
ምግቤን ያለ ድካም እንድበላ ብለህ፣
ያስተመጥከኝን ሰው ወሬ ሲደልለኝ፣
ገልቦ ሲያራቁተኝ በቸልታ አትየኝ።
አዝማች. . .

2. ልቤ እየቸኮለ፣ እግሬ ሮጥ እያለ፣
ውርደትን ለማየት ዓይኔ እየከጀለ፣
ድንበር እየጣሰ ከኃጢአት እየዋለ፣
የማታ የማታ፣ ሚዛኔ ቀለለ።
አዝማች. . .

3. የጭንጫ ቡቃያ ፈጥኖ የበቀለ፣
ፀሐይ ስትወጣ ነዶ የተቃጠለ፣
አስተምርኖል እኔን ፍሬ እንዳፈራ፣
አንሥተህ አትጣለኝ፣ የእኔ ጌታ አደራ።
አዝማች. . .

4. ችኩል ያለ ሳኦል በዓይናችህ ተንቆ፣
ብላቴናው ዳዊት ተቀብቷል ልቆ፣
ዓይኔን ግለጠው፣ ስፍራዬን ልወቀው፣
አለድሜ እንጂ ፅድጊዬን አትቁረጠው።
አዝማች. . .

Song 3-10

That I May Stay Firmly

CHORUS:

That I may stay firmly where You placed me
That You may be pleased when You come to visit me,
Oh Lord, multiply Your grace towards me.

1. Making the paradise, my dwelling place, so beautiful
That I may eat my food without any hardship
When talk deceives me while you placed me here
Don't watch me negligently while it is stripping me to nakedness.

2. My heart hastens; my feet incline to run;
My eyes long to see shame.
Crossing the borderland, spending the day with sin,
Eventually, at last my weight was made light.

3. The sprouts on the stony soil which rapidly grew up
When the sun rose, which got dried and burned.
It taught me to bear fruit.
Don't let me down after raising me up, oh, my Lord.

4. That hasty Saul was despised in your sight.
The young David was anointed and became great
Open my eyes that I may know my place.
Shorten not my life; instead make me grow.

III-11

በትዕግሥት ፀጥታ

በትዕግሥት ፀጥታ፣ በጸሎት ቆይታ፣
ድል ይገኛል ከጌታ፣
በትዕግሥት ፀጥታ፣ በጸሎት ቆይታ፣
መልስ ይመጣል ከጌታ።። } አዝ.

1. የበረታ ሰልፍ ሲከበኝ ከኋላ ከፊት፣
ቆይቼ እግዚአብሔርን ደጅ ጠናሁት፣
እርሱም ዘንበል አለልኝ፣ ሊያጸምጠኝ፣
እንባዬን በእጁ ጠርጉ፣ ቃሉን ሰጥቶ
አጽናናኝ።።

አዝማች. . .

2. ነፍስህ ስትራቆት ፍጹም ባዶ ስትሆን፣
ያለህን አራግፈህ ሰጥተህ ስታይ ራስህን፣
ያሳለፍካቸውን ድሎች አስብ፣ ተስፋህ
ይለምልም፣
ተንበርክከህ ብትቆይ ደግሞ መጻሰስህ
አይቀርም።።

አዝማች. . .

3. ከድካም የበረቱ ሰዎች፣ በድል ያለፉ፣
ከኢየሱስ በስተቀኝ በላይ የተሰለፉ፣
መንግሥታትን ድል ነሥተው ያኔ ምሽግ
የናዱ፣
የጸሎት ሰዎች ናቸው ጠላት ያርበተበቱ።።

አዝማች. . .

Song 3-11

In Patient Quietness

CHORUS:

In patient quietness, in prayerful diligence
Victory comes from the Lord
In patient quietness, in prayerful diligence,
The answer comes from the Lord.

1. When a hard battle surrounded me
I patiently waited on God.
And He leaned to the side to hear me.
Wiping my tears with His hand, giving me
His word, He comforted me.

2. When your soul is naked and completely empty.
After you have sown all you have, you would see yourself.
Think of your past victories; let your hope revive.
If you wait on your knees, you shall certainly be visited.

3. Those who were weak and recovered their strength passed into victory.
Those who lined up, on the right hand of Jesus,
They defeated kings, then knocked the fort down.
They are men of prayer who dispersed the enemies.

III-12

እስከ ዛሬ የጠበቅከን

እስከ ዛሬ የጠበቅከን፣
ከፍላጻ የሸፈንከን፣
ዳርቻችንን ያሰፋህልን፣
እንባችንን ና አብስልን።
} አዝ.

1. በማይገሰሰው ክብርህ፣
በማይመጠን ጉልበትህ፣
እንተነትህን ያሳየህ፣
ለእኛም ከለላ የሆንህ።
አዝማች. . .
2. የጠላትን ቁጣ አይተን፣
ልካችንን ስንመጥን፣
ተስፋ ቆርጠን ወዮ ስንል፣
አማኑኤል ደረስክልን።
አዝማች. . .
3. በማባበል ሊያስማማን፣
ካልተሳካም ሊያስፈራራን፣
ጠላት ሲጥር ሲያሸክብን፣
ሴራውን ያከሸፍክልን።
አዝማች. . .
4. ድብልቅ ኑሮ ያልኖረ፣
ከእግዚአብሔርም የተማረ፣
ቢማትብም ያሸንፋል፣
የአምላኩንም ስም ያስጠራል።
አዝማች. . .

Song 3-12

You Who Watched Over Us Until Today

CHORUS:

You who watched over us until today,
You who covered us from arrows,
You who broadened our borders,
Come and also wipe our tears away.

1. By Your irreproachable honor
By Your immeasurable strength
You who revealed Your being,
You have become our protection.

2. When we saw the anger of the enemy
When we measured our strength
When in despair we wailed, "Oh, dear!"
You, Emmanuel, arrived on time for us.

3. Flattering us to persuade
If he fails to threaten us,
The enemy trying to cluck on us.
You who foiled his conspiracy against us.

4. One who lives a straight (non-mixed up) life
Who has learned from God,
Though he gets weak, he will win,
He will make the name of his God well-known.

III-13

አንተን፣ አንተን ብዬ

አንተን፣ አንተን ብዬ፣
እኔን ወደ ኋላ ጥዬ፣
በእምነት እሻገራለሁ፣
በድል ፊትህን አያለሁ።። } አዝ.

1. ከቀደሙት ተምሬአለሁ ፣
የአንተን ተስፋ እጠብቃለሁ።።
በምሕረትህ ተመልከተኝ፣
እምነትንም ጨምርልኝ።።
አዝማች. . .

2. የፍየልን ሌጦ ለብሰው፣
መስቀልህን ተንተርሰው፣
የተንከራተቱ ብዙ አሉ፣
ካብራቸውን ለአንተ የጣሉ።።
አዝማች. . .

3. በእምነት ስምህን ጠሩ፣
በጸሎት ለአንተ ነገሩ፣
ከላይ ሆነህ ሰማሃቸው፣
ቃላቸውን አደመጥካቸው።።
አዝማች. . .

4. በእምነት ባሕር መጠጡ፣
ከጠላት እጅ አመለጡ፣
እነርሱን ልመስል እሻለሁ፣
በእምነት ስምህን እጠራለሁ።።
አዝማች. . .

5. ከመንፈስ መልእክትን ሰሙ፣
ጌታ አንተን ተላለሙ፣
እምነትን ስጠኝ እላለሁ፣
እኔም አንተን አለምናለሁ።።
አዝማች. . .

Song 3-13

Seeing You And You First

CHORUS:
Seeking You and You first
I will put myself last.
I will cross over by faith.
I will see Your face in victory.

1. I have learned from those who went before.
I am waiting for Your promise.
Look at me by Your mercy
Add to me more faith.

2. Clothed in goat skins
Leaning on your cross
There are many who wandered
Who left their own honor for You.

3. They called Your name by faith.
They told You everything in prayer
You heard them from above;
You listened to all the words they said.

4. By faith they dried up the sea
They escaped from the hands of the enemy.
I want to be like them;
I will call, by faith, on Your name.

5. They heard messages from the Spirit
Lord, they saluted You.
I'm asking You, give me faith,
I too, am begging of You.

III-14
ኢየሱስን ለብሰህ

ኢየሱስን ለብሰህ፣ የጦር ዕቃህን
አንሥተህ፣
በእርሱ መልካም ጦርነት ተዋጋ፣
ኢየሱስ ያሸንፋል፣ ለድሉ አትስጋ።

አዝ.

1. የሚቀጠቅጥ በአንተ ላይ ወጥቷል፣
በጠላት ተከበሃል፣
ክርስቲያን ተጠንቀቅ፣ ዙሪያህን አስተውል፣
ጉልበትህ አይላላ፣ ጠንክረህ ተዋጋ፣
ብድራትህን አይተህ ያለልህን ዋጋ።
አዝማች. . .

2. በጦርነት ላይ መቁሰልም አለ፣
ሞትም ቢሆን ጥቅምህ ነው፣
ለጨለማው ገዢ እጅህን አትስጠው።
እስከ ሞትህ ታመን፣ ነፍስህን አታክብራት፣
ለታመነው ፈጣሪ አሳልፈህ ስጣት።
አዝማች. . .

3. ባላጋራህ ዲያብሎስ ሊውጥህ፣
እያገሳብህ ነውና፣
ከድምጹ አትፍራ፣ አባትህ አለና፣
መንጋጋውን ዘግቶ ከአፉ ያስጥልሃል፣
ከቶም እንደማይተውህ በግልጽ ያሳየዋል።
አዝማች. . .

4. የውጊያው ጊዜ አሁን ነው፣ ወንድም፣
ተነሥ ተጋጠመው ድል ትነሳዋለህ፣
በርትተህ ታገለው፣
የአብርሃም አምላክ ጋሻ ይሆንሃል፣
ለአገርህም አብቅቶህ አክሊል ይሰጥሃል።
አዝማች. . .

Song 3-14
Putting On Jesus

CHORUS:

Putting on Jesus, pick up your armor.
Fight a good fight in Him.
Jesus will win. Do not doubt about the victory.

1. The one who bruises has risen against you.
Christian, take care; you are surrounded by the enemy.
Study your surroundings; let not your strength be flimsy.
Fight vigorously; see the rewards you will have; fight your best.

2. It is obvious that one gets wounded in battle.
Even death is your benefit.
Don't surrender to the ruler of darkness.
Be faithful until death. Don't give value to your soul.
Give it over to the faithful creator.

3. You enemy the devil is roaring to swallow you.
Don't be scared by his noise.
Your Father is with you; He will snatch you out of the enemy's mouth and will lock his jaws.
He will show him clearly that He will never leave you.

4. The time of war is now, brother.
Get up and fight him; you will defeat him.
Fight him vigorously; the God of Abraham will be your shield.
After He has brought you to your country
He will give you a crown.

III-15
ልብህ ጽኑ ይሁን

ልብህ ጽኑ ይሁን፣ አትላላ፣ ጠንክር፣
ባመንክበት ጌታ በፍጹም አትፈር።።
ልብህ ጽኑ ይሁን፣ አትላላ፣ ጠንክር፣
ባመንክበት ጌታ በፍጹም አትፈር።።

} አዝ.

ተድላና ደስታ፣ መጽናናት በረከት፣
ሁሉ መንደላቀቅ በተሟላ ሕይወት፣
እንደዚህ አይደለም፣ እንዲህ አትመልከት፣
ክርስትና አንዳንዴ መከራም አለበት።።
አዝማች . . .

የጨለማው ሥልጣን ጥላውን ዘርግቶ፣
ጠላት ኃይሉን ሲያሳይ እጅግ ተቆጥቶ፣
በበትር ሲመታህ ኮምጣጤ ሲያጠጣህ፣
በመስቀሉ መንገድ ወንድሜ አይክፋህ።።

አዝማች. . .

ግምለጫ ስትሻ፣ ቀዳዳ ስትፈልግ፣
ጭላንጭሉ ስንኳ ሲደፈን ሲመረግ፣
ወንጌ ተጥለህ ሰው ሁሉ ሲረሳህ፣
የሕይወትህ ጌታ የሚረሳህ አይምሰልህ።።

አዝማች. . .

ምስራች ቃሉ በወንጌል ተሟገት፣
ልብህ ሰፊ ይሁን፣ አርቀህ ተመልከት፣
ግያልፈው እርስት ለሀገርህ ተዋግተህ፣
ላይ እንገናኝ ደምህን አጥለቅልቀህ።።
አዝማች. . .

Song 3-15

Let Your Heart Be Firm

CHORUS:

Let your heart be firm; don't be soft, be strong.
Don't be ashamed of the Lord in Whom you trust.

1. Happiness and joy, comfort and blessing
Always a luxurious comfortable life –
It isn't like this; don't expect it all to be easy.
Christianity sometimes has hardships.

2. When the power of darkness casts its shadow;
When the enemy shows his strength very angrily.
When he hits you with a stick and makes you drink vinegar,
Brother, don't be disappointed on the way of the cross.

3. When you seek an escape, searching for an outlet,
Even when the least hope of light is hindered and lost
When all men forget you and you are thrown in prison,
Don't think that the Lord of your life will ever forget you.

4. Contest the enemies by the Word of Good News, the Gospel
Be patient and look at the future.
Fighting for your country for an inheritance that won't pass away
Let us meet the above overflowing with your blood.

III-16

ለረጅም ዘመናት

ለረጅም ዘመናት ተቸግሮ ማቆ፣
ክርስቲያን ተሻገር ወላፈኑን ዘልቆ።። } አዝ.

1. አብን በዙፋኑ፣ ወልድን በስተቀኙ፣
በምድር የተገፋውን በክብር ሊገናኙ።
ሲጋብዙት ታይቶ ክርስቲያን በቃሉ፣
«ተፈጸመ» ብሎ ወጣ ከሐሩሩ።

አዝማች . . .

2. እውር ፈሪሳውያን በምናቸው ይዩ፣
ጸዳል መፈጠቁን ከችግር ትይዩ፣
በመከራ ናዳ በሰዎች ጫጫታ፣
ሩጫውን አከተመ ጀግናው ሳይረታ።

አዝማች. . .

3. ከሀገር ሀገር ሲዞር ሲንከራተት ከርሞ፣
መልኩ ተቀይሮ በመከራ ክስሞ፣
ከጅራፍ ከዱላ ከጨካኞች ጡጫ፣
ክርስቲያን አንቀላፋ አረፈ ከእርግጫ።

አዝማች. . .

4. እንደነ ያዕቆብ በደም ተብከለው፣
ለወንጌል ሊደቱ ለቃል ሊጸናቸው፣
በሰልፍ ቆመዋል ተራ ይጠብቃሉ፣
ኢየሱስ፣ ኢየሱስ፣ ኢየሱስ ይላሉ።
አዝማች. . . (2 ጊዜ)

Song 3-16

After Suffering and Languishing

CHORUS

After suffering and languishing for ages,
The Christian crossed over, passing through the flame.

1. The Father on His throne; the Son on His right hand.
To meet, the One who is pushed aside on earth, in glory
When Christian saw them inviting him out of his agony
He came out of the furnace saying, "It is finished!"

2. With what would those blind Pharisees see?
That the light has penetrated through the difficulty
The massive difficulties and disturbing shouts of people
The hero has completed his race without fainting, without being overcome.

3. After wandering for some time from country to country
His appearance was changed. Tired from hardships,
From whips, from clubs, from cruel fists,
Christian passed away and rested from the kicks.

4. Like Jacob they were stained in blood.
To lay down themselves for their promise, the Gospel
They've lined up waiting for their turns,
They are saying "Jesus, Jesus, Jesus".

ካሴት ቁጥር 4

IV-1
መልክህን ጌታዬ

1. መልክህን ጌታዬ፣ ፀሐይ አጥቁሮታል፣
በሐሩሩ ብዛት ክስተህ ገርጥተሃል።
ምቾትም ድሎትም አልነበረህም ጌታ፣
ለሰብአዊው ፍጥረት በሥቃይ ተመታህ።
ምቾትም ድሎትም አልነበረህም ጌታ፣
ለሰብአዊው ፍጥረት በሥቃይ ተመታህ።

2. የሞት ጽዋ ቀርባ ፈዋሼ ሲጨነቅ፣
የአባቱ ድምፅ ርቆት በዛንቀት ሲሳቀቅ፣
አንጀቱ ተጣብቆ፣ አጥንቱ ሰልስሎ፣
የእኔን ሕይወት ዋጀ፣ ጌታዬ ተጋድሎ።
አንጀቱ ተጣብቆ፣ አጥንቱ ሰልስሎ፣
የእኔን ሕይወት ዋጀ፣ ጌታዬ ተጋድሎ።

3. ተራራ እየሳጠኽ በመዳህ ስትወጣ፣
ሆንክልኝ መድኄ ስለኔ ከርታታ።
ለአንተ የጣር ቀን ነው፣ ለኔ የፈውስ ዕለት፣
ራስህን አጋልጠህ ፈጸምከው በትዕግሥት።
ለአንተ የጣር ቀን ነው፣ ለኔ የፈውስ ዕለት፣
ራስህን አጋልጠህ ፈጸምከው በትዕግሥት።

CASSETTE 4
ENGLISH TRANSLATION

Song 4-1

Your Beauty, My Lord

1. Your beauty, my Lord, was burnt by the sun.
From the excess heat, You were lean and marred.
You had no comfort nor cosy situation, Lord.
For Your creation, You were smitten by pain. (2x)

2. As the death cup was near and my healer worried
His Father's voice was too far to reach; there He suffered
His belly so hollow, His ribs clearly seen.
By His death struggle, my Lord, my life He redeemed.

3. You climbed the hill by clinging and crawling
On my behalf, my Lord, You were made to wander.
For You a day of suffering, for me it was a day of healing.
By offering Yourself, patiently, You made it at last.

IV-2

የባዘንከው ውድ ወንድሜ

የባዘንከው ውድ ወንድሜ፣
አምጠኝ እስኪ ልምከርህ ደግሜ፣
ወደ ነፍስህ እረኛና ጠባቂ ና ተመለስ።
} አዝ.

1. በከንቱ ሮጠህ፣ ጉልበትህ ባክኖ፣ ጨርሶ አልቆ፣
በኃጢአት ሸክም ነፍስህ መንምኖ፣ አጥንትህ ደርቆ፣
መድረሻ ጠፍተህ ግራ ገብተህ የምትባዝን፣
የዓለምን ቤዛ ቀርበህ አማክረው ጌታ ኢየሱስን።
አዝ.

2. ያለማውቅን ወራት፣ ዘመናት እና ዓመታትም፣
ከኢየሱስ ውጪህ እርካታ ላይገኝ እንዲያው ስታልም፣
በዓለም የሚያገኝ ኩቶ አይገኝም፣ ምን ይሻልሃል፣
ድንቁ ኢየሱስን ተቀብለው ያረክሃል።
አዝ.

3. እውቀትን አጥተህ በዚች ዓለም ላይ የተንከራተትክ፣
በጨለማው ግዛ በዲያብሎስ እጅ የተማረክ፣
ምርኮን ለመሻረል ከላይ ከሰማይ የወረደው
የምስራቹን ትፈልጋለህ፣ አማኑኤል ነው።
አዝ. /2 ጊዜ/

Song 4-2

You Who Wander

CHORUS:

You who wander, my dear brother,
Listen and let me advise you again.
Come back to the shepherd and keeper of your soul.

1. You ran for nothing, your energy wasted, completely exhausted.
By the burden of sin, your soul was worn out, your bones dried up.
You knew not your destination – lost, you knew not what to do, but wander.
Come to the Lord Jesus; seek advice from the ransom of the world.

2. Months, ages and years of ignorance
Dreaming in vain to get satisfaction apart from Jesus
There is no one in this world who constructs and strengthens;
What, then, is best for you?
Receive the wonderful Jesus; He will satisfy you.

3. You who couldn't find knowledge, but just wandered;
Oh, victim of the devil who is ruler of darkness,
There is One who descended from heaven seeking a share of the spoils.
If you want to hear the herald, He is Emmanuel.

IV-3

ከሸካራው መንገድ እግርህን መልሰው

ከሸካራው መንገድ እግርህን መልሰው፤
እይበጅህምና ደሜን አትርገጠው፤
ይልቅ እንታረቅ ምሕረቱ ብዙ ነው።

አዝ.

1. ገና ሕፃን ሳለህ፤ ስጠነቀቅልህ፤
ክንዶችህን ይዤ፤ ዳዴ ሳስተምርህ፤
መራመድን ችለህ፤ ሩጫውን አቀላጥፈህ፤
እንዲያ የነበርከው፤ ዛሬ ግን ታከተህ።

አዝማች. . .

2. በሐሩሩ ተቃጥለህ በጥም ተመተሃል፤
ወዝህ ሁሉ ደርቆ፤ ፍሬ ቢስ ሆነሃል፤
መንፈሳዊነትህ አሁን ከንተ ርቆ፤
ለሥጋህ የተገዛህ ጸጋህ ሁሉ አልቆ።

አዝማች. . .

3. ከጥንት ጀምሬ እኔ እምላክህ ነኝ፤
በደሜ የዋጀሁህ ተው አታሳዝነኝ፤
ምሕረት እንደምወድ ፀባዬን ታውቃለህ፤
እልሁን ተውና ታረቀኝ ልጅህ ነኝ።

አዝማች. . .

4. ምሕረትህ ተነሥታለች፤ ልቤ ተናውጣለች፤
እጄ ተዘርግታ ገና ትኖራለች፤
የፍቅር ቀንበሬን ናና ልጫንብህ፤
ጫንቃህም ስጠኝ ዳግም ልረስብህ።

አዝማች. . .

Song 4-3

CHORUS:

Retreat from the Rough Road

Retreat from the rough road.
Don't step on My blood; that won't do you any good
Let's be friends instead, for My mercy is full.

1. When you were still a baby, I cared for you.
I put your hands in Mine and taught you to walk.
You learned to walk and knew how to run fast.
You were swift then, but now you have given up.

2. You are burnt by the heat and smitten by thirst.
Your oil all dried up and you have become fruitless.
Your spirituality is now departed from you.
Because you are ruled by your flesh all your grace is finished.

3. I am your God since the time in Egypt.
I am the One Who bought you by My blood.
Stop making me sad.
You know that I love mercy; this is My behavior you know.
Cease to be stubborn and be My friend, you are My child.

4. My mercy has risen; My heart is stirred.
My hand still remains outstretched.
Come, and let Me put My yoke of love on you.
Give Me your shoulder and let Me plough by you.

IV-4

ሊጠፋ የነበር፣ በኃጢአቱ ረክሶ

1. ሊጠፋ የነበር፣ በኃጢአቱ ረክሶ፣
ለጥቂት አምልጦ ከዓለም ተመልሶ፣
ማንነቱን አውቆ ልብ ገዝቶ ናሮ፣
ባለፈው ጥፋቱ በጸጸት ተማሮ፣
መጥቷል በንስሐ የጌታን ቃል ሰምቶ፣
ለይጣንን ዓለምን፣ ሥጋን ተሰናብቶ፣
መጥቷል በንስሐ የጌታን ቃል ሰምቶ
ለይጣንን፣ ዓለምን፣ ሥጋን ተሰናብቶ።።
2. እንዲያው ሲግደረደር ጥማቱን ደብቆ፣
የጭንቀቱን ግፊት በሆዱ አምቆ፣
ሰላምን ለማግኘት ሲባዝን ሰንብቶ፣
ከሰላም አለቃ መንገድ ተገናኝቶ፣
አሁን ወጥቶለታል፣ ችግሩን ተንፍሶ፣
ተጽናንቶም ይኖራል፣ ሕይወቱ ታድሶ፣
አሁን ወጥቶለታል፣ ችግሩን ተንፍሶ
ተጽናንቶም ይኖራል፣ ሕይወቱ ታድሶ።።
3. ወዶታል ከአንጀቱ፣ ተመክቶበታል፣
ጌታም በጠላት ፊት በዘይት ቀብቶታል፣
ከትቢያ አንሥቶ ሞገስን ሰጥቶታል፣
በድል አየመራው ከዚህ አድርሶታል፣
እንደ ሰባ እንሶላ በደስታ ይዘላል፣
አየፈነደቀም «ሃሌ ሉያ» ይላል።።
እንደ ሰባ እንሶላ በደስታ ይዘላል፣
አየፈነደቀም «ሃሌ ሉያ» ይላል።።
4. ጠቢባን ግንበኞች ወደ ጉን የጣሉት፣
አይጠቅመንም ብለው በንቀት የካዱት፣
የናዝሬቱ ኢየሱስ ግን የማዕዘን ዓለት፣
ሆኖለታል ለእርሱ የሕይወት መሠረት።።
ከዳንኩኝስ ብሏል አዲስ ሰው ከሆንኩኝ፣
ዘመድ ወዳጆቼ ያሉትን ይበሉኝ።።
ከዳንኩኝስ ብሏል አዲስ ሰው ከሆንኩኝ፣
ዘመድ ወዳጆቼ ያሉትን ይበሉኝ።።

Song 4-4

The One Who was About to Be Lost

1. The one who was about to be lost, defiled by sin,
Barely escaping from the world,
Realizing who he was and becoming wise,
He bitterly confessed his wrong doings from the past.
He has come back in repentance heeding the Lord's words.
He bade farewell to Satan, the world, and the flesh. (Repeat last 2 lines)
2. My hypocritically hid his thirst.
The pressure of his troubles internally suppressed,
He tarried wonderingly, looking for peace.
He then met the Prince of Peace on the way.
Now he's freed, relieved from his problems,
And he's living comfortable with a life renewed. (Repeat last 2 lines)
3. He loves him full-heartedly and is proud of him.
The Lord has anointed him with oil in the presence of his enemies.
He has raised him up from dust and covered him with honour.
Leading him into victory, He brought him thus far.
Like a fattened calf, he jumps up with joy.
"Hallelujah" he shouts with gladness and joy. (Repeat last 2 lines)
4. The stone thrown aside by wise builders
Saying "It is useless for us", they despised and denied it.
But Jesus of Nazareth is the Cornerstone.
He has become for him the foundation of life.
He said, "Since I am saved and became a new creation"
Let my relatives and friends say whatever they like. (Repeat last 2 lines)

IV-6
የፈርዖን ገንዘብ ያልማረከው ጀግና

1. የፈርዖን ገንዘብ ያልማረከው ጀግና፣
ኃይሉ ያልደከመ ያላለተ ገና፣
ድል ለማድረግ ወጣ በጦርነት ሊቃ፣
በጀርባው አንግቦ የአምላኩን ጦር ዕቃ።
ድል ለማድረግ ወጣ በጦርነት ሊቃ፣
በጀርባው አንግቦ የአምላኩን ጦር ዕቃ።

2. የወህኒው እስራት የግርፋት ብዛት፣
አልቻለም ሊያበርደው የፍትሩን ትኩሳት።
ፎክረ ያ ጉብል ሊጥል ሊገረስስ፣
ጠምዶ በቀኝ እጁ የቃሉን መትረየስ።
ፎክረ ያ ጉብል ሊጥል ሊገረስስ፣
ጠምዶ በቀኝ እጁ የቃሉን መትረየስ።

3. የልብ ዓይኑ ፈጦ ትኩር ብሎ እያየ፣
የጠላትን ምሽግ ሰፈሩን አጋየ።
የአርያም አሳት በኃይል ጉብኝቶታል፣
አባብና ጊንጡን ከእግሩ ሥር ረግጦታል
የአርያም አሳት በኃይል ጉብኝቶታል
አባብና ጊንጡን ከእግሩ ሥር ረግጦታል።

4. ከድካም በረታ ጅማቱ ጠንክሯል፣
አንገብግቦት ፍትሩ ወኔው ተቀስቅሷል።
በጀርባው መተልተል ጌታን አከበረ፣
የሞትንም ባሕር በእምነት ተሻገረ።
በጀርባው መተልተል ጌታን አከበረ፣
የሞትንም ባሕር በእምነት ተሻገረ።

Song 4-6
The Hero Who Was not Attracted by Pharaoh's Riches.

1. The hero who was not attracted by Pharaoh's riches.
His strength was not weakened and still was not drained
He went out to win in anger of battle
Carrying his God's weapon on his back. (2x)

2. The prison fetters and heavy lashes –
They couldn't cool down his warmth of love.
The young strong man threatened to smash and knock.
He has loaded his right hand with his automatic words. (2x)

3. With his heart's eye widely open and staring,
He set his enemies' camp on fire.
The fire of heaven has visited him mightily.
He stamped snakes and scorpions under his feet. (2x)

4. He is strengthened and his muscles are strong,
The love is burning him, he is encouraged.
He glorified the Lord by the wounds of his back,
He crossed the river of death by faith.
He glorified the Lord by the wounds of his back,
He crossed the river of death by faith.